# ሐዲስ



19ኛ ዓመት ቁጥር 63

መስከረም ወር 2017 ዓ.ም



## “የአርብ ጠንካራ እጆች የወባ ወረርሽኝን ይገታሉ!”

### አብክመ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ

## ራዕይ

በመረጃ የበለፀገ፣ ሁለገብ ተሳትፎ የሚያደርግ፣ በመሠረታዊ ክልላዊና አገራዊ ጉዳዮች መግባባት የፈጠረ ህዝብ በ2022 እውን ሆኖ ማየት

## Vision

To see a society with rich information and all rounded active participation for a better understanding on fundamental regional and country level affairs for having common consensus in 2030

## ተልዕኮ

በመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ኢንፎርሜሽንና ሚዲያ ዘርፍ መሪ ሚና በመጫወት በህብረተሰቡ መካከል ውጤታማ የመረጃ ልውውጥ በማድረግ በመሰረታዊ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ ዕቅዶችና ፕሮግራሞች ዙሪያ የመላውን ህዝብ ግንዛቤ በማዳበር ሁለንተናዊ እድገታችንን ወደ ላቀ ደረጃ በማሸጋገር ለራዕያችን ስኬታማነት የተቀናጀ ርብርብ ማድረግ፣

## Mission

playing a leading role in government communication information for a successful information exchange with in a society. to enhance the awareness of the people on the fundamental government policies strategies. plans and programs for a better step of succession our vision by stron collaboration.

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን ቢሮ በየ 3 ወሩ የሚዘጋጅ መጽሔት

የመስከረም ወር 2017 ዓ.ም

19ኛ ዓመት ቁጥር 63

# ሐዳስ

## አዘጋጆች

- ፍሬው ምናለ
- ይበልጣል መኮነን
- ሲሳይ ጌቴ
- ደፋሩ እምሬ

### አርታኢ

- ጋርዳቸው አንሙት
- ፈቃዱ ገድፍ

### ህትመት ስርጭትና ክትትል

- ደባሱ ካሣ

### ግራፊክስ ዲዛይን

- ጌታሁን ላቀ

ገጽ

የቢሮ ኃላፊው መልዕክት፡-

ደብዳቤዎች፡-

ፖለቲካ/መልካም አስተዳደር፡-

ሰሚ ያጣዉ . . . ........................................................9

ልማት/ኢኮኖሚ፡-

የፀና የትዉልድ ዉርስ .................................................... 14

ባህል/ ታሪክ፡-


ምርጥ ምርጡን ........................................................19

ማህበራዊ፡-

የዘርፉ እምርታዎችና ተግዳሮቶች ..................................24

ልዩ ልዩ

ስለ አለቃ ገብረሃና በጥቂት ................................. 29




ውድ አንባቢያን መጽሔታችንን በማንበብ አስተያየታችሁንና መልዕክቶቻችሁን በሚከተሉት አድራሻዎቻችን ይላኩልን


Facebook. amhara communications

ስልክ- 058 220 09 40 ፣ 058 226 5921፣ 058 220 4107

ፋክስ- 058 220 1105 / 058 226 4172

ኢሜል- anrsnproduction@ gmail. com

ዩቲዩብ- www.youtube.com/ANRS communication af fairs office

ቲውተር- www.twitter.com/ANRS GCAO

ዌብሳይት- www.amharainfo.gov.et

ፖ.ሣ.ቁ 607


የዝግጅት ክፍሉ



የጤናው ዘርፍ የልማት እና የኢንቨስትመንት ዕቅድ ሁለተኛ አመት የትግበራ ዘመን ላይ ሲሆን እየቀጠሉ ያሉ የጸጥታ ችግሮችን፤ ወረርሽኞችና ሌሎች ተፈጥሮአዊ አደጋዎች ያስከተሏቸውን ተጽዕኖዎች በመቋቋም የማይበገር የጤና ስርዓት ከመፍጠር አንጻር መልካም ውጤቶች ተመዝገበዋል። ቢሮው አዳዲስ ኢኒሼቲቮችን ማስጀመር የቻለ ሲሆን  የጤና ተቋማትን ጽዱና ለተገልጋዮች ሳቢ ለማድረግ ትኩረት ተሰጦት እየተሰራ ሲሆን እስካሁን ባለው ሂደት 212 ጽዱ የጤና ተቋም መፍጠር ተችሏል። የድጅታል ጤና ስራ በተለይ ወረቀት አልባ የህክምና ስርአት በ7 ጤና ጣቢያና ሆስፒታል የተተገበረ ሲሆን ቀጣይ ወደ ሌሎች አካባቢዎች ለማስፋትና ለዚሁ አገልግሎት የሚውሉ ኮምፒውተሮችን ለማግኘት እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል። በጤና ኬላ ደረጃ የመረጃ ስርአቱን የማዘመን ስራ እየተሰራ ሲሆን በ86 ወረዳዎች በታብሌት የማህበረሰብ መረጃ ስርአት ተጀምሯል። በ148 የጤና ተቋማት ለኦዲት የተመቸ የፋርማሲ አገልግሎት ትራንዛክሽን (APTS) ከመጀመሩ ባሻገር እንደ ክልል 33 የማህበረሰብ አቀፍ መድሀኒት ቤቶችን ስራ ማስጀመር የተቻለ ሲሆን አገልግሎት ለመስጠት በዝግጅት ላይ ያሉ 39 የማህበረሰብ አቀፍ መድሀኒት ቤቶች ይገኛሉ።በ106 ጤና ጣቢያ ለነፍሰ ጡር እናቶች አልትራሳውንድ እንዲኖር በማድረግ ሪፈራልን የሚቀንስ አገልገሎት መስጠት ተችሏል። ሆስፒታል በሌለባቸው ወረዳዎች በጤና ጣቢያ ደረጃ 117 የመለስተኛ ቀዶ ህክምና የሚሰጡ ግንባታዎች ተጀምረው 104ቱ ግንባታቸው ተጠናቋል፤ ከእነዚህ ውስጥ 27ቱ ለወላድ እናቶች የቀዶ ህክምና አገልግሎት መስጠት ጀምረዋል። በ58 አጠቃላይ ጤና ኬላ እና 268 መሰረታዊ ጤና ኬላ ከጤና ጣቢያ ባለሙያ በጊዜያዊነት በመመደብ እንዲጀምሩ ተደርጓል። የወባ በሽታ ስርጭትን በመከላከል ረገድ "ጤና ጣቢያ መር የማህበረሰብ አቀፍ የወባ መራቢያ የአካባቢ ቁጥጥር" ስራ በየደረጃው በንቅናቄ መምራት ተጀምሯል፤ በዚህም ተስፋ ሰጪ ውጤቶችን ማየት ተችሏል። የክልሉ ጤና ቢሮ ካመጣቸው አዳዲስ ኢኒሼቲቮች መካከል አንዱ የሆነው የጤናው ዘርፍ የአመራር ስልጠና /Health System Leadership Induction and Guiding Training/ በጤናው ዘርፍ የአገልግሎት አሰጣጥን ለማሻሻል እና ቀጣይ የጤና መሪዎችን መፍጠር በሚያስችል አግባብ 585 ተሳታፊዎች ስልጠናቸውን ወስደው አጠናቀዋል።

አቶ አብዱልከሪም መንግስቱ

የአብክመ ጤና ቢሮ ኃላፊ



በሀገር አቀፍ ደረጃ የንግድና ገበያ ልማት ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በህግና በስርዓት እየተመራ ለሀገር ዕድገት ማበርከት ያለበትን ታላቅ ሚና እንዲወጣ በትኩረት እየተሰራ ነዉ፡፡

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስትም የንግድና ገበያ ልማት ቢሮ በክልሉ ፍትሃዊ የንግድ አሰራርና ዘመናዊ የንግድ ስርዓትን በመዘርጋት ብሎም መልካም አስተዳደርን በማስፈን የንግዱንና የሸማቹን ማህበረሰብ ተጠቃሚነት በማረጋገጥ የእርካታ ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግ ሰፊ ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ለዚህም ቢሮው በክልሉ ህጋዊ የንግድ ስርአት እንዲጎለብት፣ ጥራቱን የጠበቀ ምርትና አገልግሎት ለህብረተሰቡ እንዲደርስ የግብይት ትስስር በመፍጠር፣ የገበያ መሰረተ-ልማቶችን በማስፋፋትና ወቅታዊ የገበያ መረጃ ስርዓት በመዘርጋት ለኤክስፖርት ግብይት መጎልበት ሁለንተናዊ ድጋፍና ክትትል በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ በተጨማሪም ቢሮው አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን በመዘርጋት ህጋዊና ተወዳዳሪ የንግድና ግብይት ስርዓት ለማጎልበት አልሞ በመስራት ላይ ነው፡፡ በተለይ ደግሞ የግብይት ተዋናዮችን በአደረጃጀት፣ በአሰራር፣ በግንዛቤ፣ በካፒታልና በመስሪያ ቦታ እንዲጠናከሩ በሚያደርግ አግባብ ለመምራት ቢሮው አቅጣጫ አስቀምጦ እየተንቀሳቀሰ ነው፡፡ ከዝርዝር ተግባራት መካከል ዋና ዋናዎቹ ለጅምላ ንግድ ፈቃድ ትኩረት በመስጠት የንግድ መሰረቱን ለማስፋት ለነጋዴዎች የንግድ ስራ ፈቃዳቸውን ማደስና  እና አዲስ የንግድ ስራ ፈቃድ መስጠት፣የንግዱ እንቅስቃሴ ህጋዊ አሰራሩን ተከትሎ የንግድ ውድድርን ጤናማ በማድረግ ህጋዊነትን በማስፋት የሸማቹን ደህንነትና ተጠቃሚነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ተግባራት ተከናውነዋል፡፡ በተለይ ያልተገባ ዋጋ መጨመር፣ የምርት እንቅስቃሴ መስተጓጎልና ያለንግድ ፈቃድ መነገድን ለመከላከል ትኩረት ሰጥቶ  መስራት፣ አምራችና ሸማቹን የሚያገናኙ የገበያ ማዕከላትን በማስፋፋት ግብይቱን ጤናማና ተደራሽ በማድረግ ያልተገባ የዋጋ ጭማሪንና የደላላ ጣልቃ ገብነትን በመከላከል ዋጋ ለማረጋጋት የገበያ ማእከላት ወሳኝ ናቸዉ፡፡ሆኖም ባለፉት አመታት እነዚህ መሰረተ ልማቶች ትኩረት ያላገኙ በመሆኑ በዚህ ዓመት በክልላችን ከመንግስት በተሰጠው የትኩረት አቅጣጫ መሰረት በበጀት ዓመቱ ስምንት ደረጃቸውን የጠበቁ በመንግስት ካፒታል በጀትና በሪጅዮ ፖሊታን ከተሞች መቀናጀ በጀት እና 75 የሚሆኑ በመለስተኛና አነስተኛ ከተሞች ደግሞ በራሳቸው  የህብት አቅም የሚገነቡ የእሁድ ገበያዎችን አቅም የማጠናከር ስራ እየተሰራ ነዉ፡፡ በተጨማሪም የሰብል፣ ኢንዱስትሪ እና የእንስሳት ወውጤቶች ግብይት ለማሳለጥ የተዘዋዋሪ ብድር በማቅረብ፣ በግብይት ተዋናዮች መካከል ትስስር በመፍጠርና በቅንጅታዊ አሰራሩ ዙሪያ ግንዛቤያቸውን በማሳደግ ለመንግስት ሰራተኛውና ለከተማው ነዋሪ ምርት ለማቅረብ ጥረት ማድረግ፣ ለውጭ ንግድ በመሸኛ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ግኝት ማሳደግ እና የመሳሰሉት በያዝነው በጀት ዓመት ትኩረት ተሰጥቶ የሚሰሩ ተግባራት ናቸው፡፡

ኢብራሒም መሐመድ (ዶ/ር )

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ንግድና ገበያ ልማት ቢሮ ኃላፊ



የአብክመ የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት የክልሉን የጤና ደህንነት በማስጠበቅ እና የበለጠ በማሻሻል ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እየፈጸመ ይገኛል፡፡

ኢንስቲትዩቱ በክልል አቀፍ የህብረተሰብ ጤና ምርምር አጀንዳዎች ላይ ተመስርቶ ቅድሚያ ትኩረት በተሰጣቸው የጤና ችግሮች ላይ የጥናትና ምርምር ስራዎችን በማካሄድ የሳይንሳዊ ኢኖቬሽንና ቴክኖሎጅያዊ እውቀትን በማመንጨት፣ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች መከላከልና ቁጥጥር ስራዎችን በማስተባበርና በመምራት ሊደርስ የሚችለውን አደጋ አስቀድሞ መከላከል፣ ሲከሰትም አፋጣኝ ምላሽ መስጠት፤ የክልሉን የጤና እና የስነ-ምግብ ላቦራቶሪዎች አቅም መገንባትና ጥራት ያለው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል ይሰራል፡፡ ተቋማዊ አቅምን በማጎልበት ዘመኑን የዋጀ ክልላዊ ጤና እና ጤና ነክ መረጃዎች ቅመራ፣ ትንተና እና አስተዳደር ማዕከል በማደራጀት መረጃ መር ውሳኔን ባህል ለማድረግ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ውስጥ ይገኛል።

በክልሉ የሚከሰቱ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋዎች ጎርፍ፣ ድርቅ፣ ጦርነት፣ የምግብ እጥረት እና ወረርሽኝ ወባ፣ ኮሌራ፣ ኩፍኝ እና ሌሎችም በሰውና በንብረት ላይ የከፋ ጉዳት እንዳያደርሱ ማድረግ የሚያስችል የዝግጁነት፣ ቅድመ ማስጠንቀቂያ፣ ምላሽ እና የመልሶ መቋቋም ተግባራትን ያከናውናል።

ኢንስቲትዩቱ በክልሉ እና ከክልሉ ውጭ በተከሰቱ ግጭቶች ምክንያት ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የሀገር ውስጥ እና ውጭ (የሱዳን ስደተኞች) ተፈናቃዮች የችግሩን ተፅዕኖ ለመቀነስ የክልሉ ተቋማትን እና አጋር አካላትን በማስተባበር የህክምና ቁሳቁስ ለጤና ተቋማት በማቅረብ፤ በጊዜያዊ መጠለያ ጣቢያዎች ላይ የሕብረተሰብ ጤና አደጋዎች ማሳለጫ ማዕከል /EOC/ በማቋቋም ባለሙያ፣ አንቡላስ እና ቁሳቁስ በመመደብ መሰረታዊ የህክምና፣ የስነ-አዕምሮ፣ የስርዓተ-ምግብ ልየታ እና የማህበራዊ ስነ- ልቦና አገልግሎት ይሰጣል፡፡

በክልሉ የጤና እና ጤና ነክ ችግሮችን በመለየት የምርምር ስራዎችን በመስራትና በማስተባበር፤ የተሰሩ ምርምሮች ጥቅም ላይ እንዲውሉ እና ለውሳኔ ሰጭ አካላት እንዲጠቀሙበት ለማድረግ እየሰራ ሲሆን የበለጠ የክልሉን የህብረተሰብ ልማት እንዲሻሻል ለማድረግ የአስር ዓመት መሪ እቅድ /2013-2022 በጀት

ዓመት/ በማዘጋጀት ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በተከታታይ ዓመታዊ ዓለም አቀፍ የምርምር ጉባኤዎችን እና በአገር ደረጃ የመጀመሪያ የሆነውን ዓመታዊ የላቦራቶሪዎች ፌስቲቫል በማካሄድ የጤና አገልግሎት ክብካቤን ከሳይንስ ጋር እንዲዘምንና ትኩረት እንዲያገኝ ከማደረግ ባለፈ የጤና ቱሪዝም በክልሉ እንዲታወቅና መሰረት እንዲይዝ ጥረት እያደረገ ይገኛል። ኢንስቲትዩቱ እነዚህ እና ሌሎች በርካታ ተግባራትን ከማከናወኑም በላይ ከክልላዊ ተቋምነት ያላፈ ስትራቴጅክ ተቋምና የዓለም ህዝቦች ሀብት ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ የዓለም የሕብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩቶች ማህበር (IANPHI) አባል በመሆን ዓለም አቀፍ ትስስሩን ጀምሯል፡፡

በአሁኑ ወቅት በክልላችን የወባ ወረርሽኝ በበተለይም በምዕራቡ ክፍል ባሉ ወረዳዎች በምስራቁ ክፍል ደግሞ ጥቂት ወረዳዎች ላይ የህበረተሰቡ ችግር ሆኗል። አሁን እየቀነሰ ቢመጣም የኮሌራ ወረርሽኝ የክልላችን የህብረተሰብ ጤና ችግር ነው። አንድም የኮሌራ ህሙም በክልላችን ከተገኘ ወረርሽኝ በመሆኑ ሁሉም ባላደርሻ አካላት ርብርብ ማደርግ ይገባቸዋል። የአጣዳፊ የስርዓተምግብ እጥረት፣ ኩፍኝ፣ የእከክ  እና ሌሎች የውሃ ወለድና ከድርቅ ጋር የተያያዙ በሽታዎች ተፈናቃይ ወገኖች በሚገኙበት የመጠለያ አካባቢ መሰረታዊ የጤና አገልግሎት በመሰጠት የከፋ የጤና ችግር እንዳይደረስባቸው መረባረብ ይገባል።

የወባ በሽታን በሚመለከት በክልላችን እና እንደአገርም 10 ቀዳሚ ከሆኑ የህመምና የሞት ምክንያቶች ዝርዝር እንዲወጣ በማስቻል ትልቅ ወጤት ማግኘት ተችሎ የነበረ ቢሆንም በቅርብ ዓመታት የወባ በሽታ እንደገና በማንሰራራት ከፍተኛ የህብረተሰብ  የጤና ችግር ሆኗል። ይህንን የበሽታ ስርጭት ሁኔታ ሁሉም በመተባብር ተገንዝቦ መቆጣጠር እስካልተቻለ  ድረስ የማህበራዊ፣ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጫና ማስከትሉ አይቀሬ ነው። በመሆኑም ኢንስቲትዩቱ ችግሩን ቀድሞ በሳይንሳዊ ትንታኔ መተንበይና በመገንዘብ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር የተለያዩ ተግባራትን እያካሄደ ይገኛል። ወቅታዊ የሆነውን ወረርሽኝ ከቁጥጥር ውጪ እንዳይወጣ በክልሉ የህብረተሰብ ጤና አደጋዎች ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል የክስተት አስተዳደር ስርዓት በማቋቋም ጥብቅ ክትትል እያደረገ ይገኛል። የወባ በሽታ ቅኝትን በማጠናከር ሰዎች የበሽታው ምልክቶች ሲታዩ በፍጥነት በጤና ድርጅቶች በመገኘት ምርመራና ህክምና ማግኘት እንዲችሉ፣ የግብዓት አቅርቦት እንዲኖር፣የተገኘን አጎበር በአግባቡ መጠቀም እንዲኖር፣ከህገወጥ ተግባራት ጋር ተያይዞ የቁጥጥር ስራዎች እንዲጠናከሩ፣ወቅታዊና የተሟላ ሳምንታዊ ሪፖርትና ግበረመልስ እንዲጠናከር እና በአጠቃላይ ስለበሽታው ሙሉ ግንዛቤ ህብረተሰቡ እንዲያገኝ ሚንስትሪም ሚዲያውም ሆነ ማህበራዊ ሚዲያው ስለበሽታው መከላከልና ቁጥጥር አተኩሮ እንዲሰራ ከማድረግ አንጻር ከፍተኛ እንቅስቃሴ እየተደረገ ይገኛል።

ሆኖም አሁንም የወባ በሽታ በከፍተኛ ሁኔታ እየተሰራጨ ስለሚገኝ በተለይም እሰከ ታህሳስ ወር መጨረሻ ድረስ የወባ በሽታ አስተላላፊ ትንኞች መራቢያ ቦታዎችን ማለትም ውሃ ያቆሩ ቦታዎች፣ በተሰባበሩ ወሃ ያያዙ እቃዎች፣ዲቾችና ጉርጓዶች፣ለቤት መስሪያ ተብሎ የውሃ ማጠራቀሚያ ገንዳዎች፣በመስኖ አካባቢና ረግረጋማ ቦታዎች የተቆራረጡ  ወሃዎች የማፋሰስና የማዳረቅ ስራዎች መተግበር አለባቸው።ይሄን ስራ የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ ሁሌ አርብ ጠዋት ጠዋት ‘’ የዓርብ ጠንካራ እጆች የወባ ወረርሽኝን ይገታሉ” በሚል መሪ ቃል የጤና ጣቢያ መር ማህበረሰብ አቀፍ የአካባቢ ቁጥጥር ስራ በይፋ በክልላችን በሁሉም ወባ ቀበሌዎች እንዲተገበር ተውስኗል። በዚህ ክልላዊ ተግባር አበረታች ጅማሮዎች ቢኖሩም የበለጠ ማጠናከርና ሁሉም ማህበረሰብ እንዲተገብርው ርብርብ ማድረግ ይገባል። በርካታ የዓለም አገሮች ወባን ማስወገድ የቻሉት በተቀናጀ የአካባቢ ቁጥጥር ስራ እንደሆነ የምርመር ጥናቶች በማስረጃነት እንደተሰነዱ ይታወቃል። ክልላችን ብሎም አገራችን ይሄን የዓለም ተሞክሮ በመውሰድ ልንሰራለትና ውጤት ልታስመዘግብበት ይገባል።

በመጨረሻ በክላልችን ከወባ በተጨማሪ ሌሎች አዳዲስ በሽታዎች እና እንደገና የሚያገረሹ በሽታዎች ሊከሰቱ ስለሚችሉ ተቀናጅተን በመስራት የከፋ ህመምና ሞት ሳያደርሱ ለመከላከልና ለመቆጣጠር ሁሌም ዝግጁ መሆን ይገባናል። የጤና ባለሞያዎች፣ የጤና ድርጅቶች እና የጤና ግብዓቶች ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆን እንዲችሉ እና ሰዎች የጤና አገልግሎት በየትኛውም ሁኔታና ቦታዎች ሁሉ የማግኘት መብቶች በዓለም ዓቀፍ ስምምነቶች፣መርሆዎችና ህጎች የተጠቀሱና   ሳይጣሱ እንዲተገበሩ የተመላከቱ በመሆናቸው ሁሉም አካላት ያለምንም ጫና እና ተጽዕኖ እንዲፈጸሙ ህብረተሰባዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

አቶ በላይ በዛብህ

የበአብክመ የህበረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ዋና ዳይሬክተር

# ሰሚ ያጣው . . .

**በሲሳይ ጌቴ**

የአገልግሎት አሰጣጥ ሥራ አመራርና ውጤታማ የደንበኛ አገልግሎት አሰጣጥና አያያዝ ለአንድ ተቋም ህልውና እንደ መሠረታዊ ነገር ይቆጠራል፡፡ ይሁን እንጅ መሠሰረታዊነቱ በበርካታ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ዘንድ በቂ ግንዛቤ ባለማግኘቱ ምክንያት በተቋማቱ ውስጥ የሚሠሩ ሠራተኞች ዘመናዊ የተገልጋዮች ወይም የደንበኞች አገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓትን ያለመረዳት ችግር ይታያል፡፡ እነዚህ የአገልግሎት አሰጣጥና የተገልጋዮች አያያዝ ችግሮች መፍትሔ የሚሹ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ጥራት ያለው የደንበኛ አገልግሎት አሰጣጥና አያያዝ ወጥነት በተሞላበት መንገድ መያዝና ማስተናገድ ይገባል፡፡የባለጉዳይ (የደንበኛ) አያያዝ የማያቋርጥ ሃደት ነው፡፡ አገልግሎት ሰጪዎች ስራቸውን እንዴት ያከናውናሉ? በምን ዓይነት ፍጥነትና ጥራት ነው የአገልግሎት ሂደቶችን የሚፈፅሙት? ለተገልጋዮች ታማኝነታቸውን ለማሣደግ የሚወስዷቸው እርምጃዎች ምን ያህል ውጤታማ ናቸው? የሚሉት ነጥቦች የአንድን ተቋም የአገልግሎት አሰጣጥ መሣካት የሚወስኑ ናቸው፡፡ የባለጉዳዮች (የደንበኞች) አገልግሎት ባለጉዳዩ ፍላጐቱን የሚወስንበትና የፈለገውን የሚያገኝበት መሃከል ያለ ሁኔታ ነው፡፡ ብዙዎቹ እንደሚገምቱት የባለጉዳዮች አያያዝ ጥራት አገልግሎቶችን ወይም ዕቃዎችን ለተገልጋይ ኀብረተሰብ ማቅረብ ብቻ አይደለም፡፡ ይህ ጥበብ አገልግሎት ፈልጐ ወደ አገልግሎት ሰጪ ተቋም የመጣውን ወይም የሚመጣውን ግለሰብ ወይም ድርጅት (ተቋም) የሚፈልገውን ለይቶ በማወቅ የተሟላ መስተንግዶ (አገልግሎት) መስጠትን ያጠቃልላል፡፡

እየጨመረ ከመጣው አገልግሎት ፈላጊ ጋር የሚጣጣም ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መገንባት ያስፈልጋል። በተቋማት ግንባታ አሰራር ሂደት ውስጥ የሰው ኃይልና መዋቅር ወሳኝ ሲሆኑ የተቋማት መሪዎች ቢቀያየሩም ዘላቂ የአሰራር ሥርዓት ከተዘረጋ በአገልግሎቱ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አይኖርም። ግልጽና ቀልጣፋ አገልግሎት አሰጣጥ አለመኖር ለሙስና እና መሰል እኩይ ተግባራት ተጋላጭ ስለሚያደርግ ቴክኖሎጂን መሰረት ያደረገ አሰራር መተግበር ወሳኝ ነው።

ስለሆነም የሐዲስ መጽሔት ዝግጅት ክፍል በባህርዳር ከተማ አስተዳደር ከተማና መሰረተ ልማት መምሪያ በመገኘት የደንበኞ አገልግሎት አሰጣጥና እርካታን በተመለከተ ከሁለት ባለጉዳዮችና ከመምሪያው የመሬት ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጂ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እንደሚከተለው አዘጋጅተነዋል፡፡ መልካም ንባብ፡፡

አቶ ሆነ ጫኔ የባህር ዳር ከተማ ነዋሪ ናቸው፡፡ ወደ ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ከተማና መሰረተ ልማት መምሪያ ተቋም መመላለስ ከጀመሩ አስር ዓመታት ተቆጥሯል፡፡ ዛሬም ልክ እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ የመጡበት ጉዳይ ሳይፈጸምላቸው ሲመለሱ በር ላይ ተገናኘን፡፡ ፊታቸው ላይ ብስጭትና ንዴት በግለጽ እየታየባቸው የመጡበትን ጉዳይ እንዲህ ይገልፃሉ፡፡ ወደዚህ ተቋም የመጣሁበት ምክንያት የቦታ ልኬታ ቅሬታ ለማቅረብ ነበር፡፡ ወደዚህ ተቋም በተመላለስኩበት ወቅት ባለሙያዎች ከስራ ቦታቸው የማይገኙበት ጊዜ ስለሚበዛ የለአግባብ ጊዜየን እያቃጠልኩ እመለሳለሁ፡፡

ከብዙ ድካም ሲገኙም ቅሬታየን እንዲፈቱ ስጠይቃቸው "ይህ ጉዳይ እኔን አይመለከትም፤ ለእኔ አይደለም የተመራ እብዛኛው ቢሮ ሂድ" እያሉ ያንገላቱኛል፡፡

እንዲሁም በተቋሙ ውስጥ ወጥነት ያለው አሰራር እንዲሁም ችግርን የሚረዳ አመራርና ባለሙያ ባለመኖሩ ያለምንም መፍትሔ እመላላሳለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አድካሚ የሆነ አሰራር ስላለ አንድን ጉዳይ በቀላሉ ማስፈጸም አይቻልም፡፡ የእጂ መንሻ መክፈልና በደላሎች በኩል ማስፈጸም የሚችል አቅም ቢኖረኝ እስካሁን መመላለስ ቀርቶ በአንድ ጀንበር ብቻ ይፈታልኝ ነበር፡፡ በቀጠሮ ብዛት ላላስፈላጊ እንግልትና ወጭ ማለትም የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት ኪሳራ እየደረሰብኝ ነው፡፡ አገልግሎት አሰጣጡ ከጊዜ ወደጊዜ መስተካካልና መሻሻል ሲገባው የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራሩ የበለጠ እየተዳከመ መጥቷል፡፡

በመጨረሻም የሚሰማ አካል ከተገኘ ቢያንስ ከስራ ቦታቸው በሰዓቱ በመገኘት በቅንነትና በታማኝነት ማገልገል ቢችሉ የማህበረሰቡን እንግልትና ስቃይ መቀነስ ይቻል ነበር፡፡ ከሚከፈላቸው ደሞዝ ውጭ ሌላ ያልተገባ ጥቅም የሚፈልጉ ባለሙያዎችና አመራሮች የተፈጠሩበትና የመጡበትን ማህበረሰብ በቅንነተና በታማኝነት ማገልገል እንደማይፈልጉ ተገንዝቤያለሁ ሲሉ ሃሳባቸውን አጋርተዋል፡፡

ሁለተኛው ያነጋገርናቸው ባለጉዳይ ደግሞ መምህር የኔአለም አጥናፉ ይባላሉ፡፡ የባህር ዳር ከተማ ነዋሪ ሲሆኑ በአዲሱ የመሬት ልኬታ መሰረት የቤታቸውን ካርታና ፕላን ለማውጣት ወደ ባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ከተማና መሰረተ ልማት መምሪያ ተገኝተው የተቋሙ የአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ያለቸውን ቅሬታ እንዲህ ይገልፃሉ፡፡

ወደ ተቋሙ መምጣት ከጀመርኩ ለአምስተኛ ጊዜ ቢሆንም ከዚህ በፊትም ለተመሳሳይ ጉዳይ መጥቸ መስተናገድ ባለመቻሌ በቅጣት ጉዳዩን አሰፈጸምኩ፡፡ አሁንም ቢሆን ሰራተኞች በስራ ቦታቸው የስራ ሰዓት በማክበር ቢሮ ገብተው በአግባቡ እያስተናገዱን አይደለም፡፡ ከስራ ቦታቸው ከገቡ በኋላም ቢሆን ተገቢውን አገልግሎት አይሰጡም፡፡ በምን መንገድ እንደሚያስፈፅሙት ባላውቅም ከበኋላችን መጥተው ቅድሚያ ተስተናግደው የሚሄዱት ብዙ ናቸው፡፡

እኛ እዚህ የምንገላታው ህጋዊ አገልግሎት ለማግኘት አስበን ነው፡፡ ስራችን ትተን እየመጣን ላልተፈለገ የጊዜ፣ የገንዘብና የጉልበት ወጭ እየተዳረግን ነው፡፡ የመጣንበትን ጉዳይ በአግባቡ ተረድተው ማስተናገድ ባለመቻላቸው ለቅጣት እንዳረጋለን፡፡አገልግሎት አሰጣጣቸው በሌላ ጉዳይ መጥቸ ባላውቅም በመጣሁበት ጉዳይ ላይ ግን እጅግ የወረደ ነው፡፡ የያዝነው ቅሬታ ወይም ጉዳይ በአግባቡ ተቀብሎ ማስተናገድ ላይ ከፍተኛ ችግር አለ፡፡

ተቋሙ ከፍተኛ የሆነ የህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ እንደመሆኑ መጠን ባለቤት ያለው አይመስለኝም፡፡ ከአገልግሎት አሰጣጡ ባሻገር የሚመጡት ባለጉዳዮች የሚያርፉበት የእንግዳ ማረፊያ የሚሆን ወንበር በቂ አይደለም፡፡ በዋናነት ደግሞ የባለሙያው የሰዓት አከባበር በእጅጉ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል በማለት ሃሳባቸውን አጠቃለዋል፡፡

የሐዲስ መጽሔት ዝግጅት ክፍል የሁለቱን ግለሰቦች ቅሬታ ጨምሮ አገልግሎት አሰጣጣቸው እና የደንበኞች እርካታን በተመለከተ ከባህር ዳር ከተማ አስተዳደር ከተማና መሰረተ ልማት መምሪያ የመሬት ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጂ ከአቶ ወንዳለ ጋሻው ጋር ቆይታ አድርገን የሚከተለውን ሃሳብ ይዘን ቀርበናል፡፡



የከተማና መሰረተ ልማት መምሪያ የመሬት ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጂ

አቶ ወንዳለ ጋሻው


በመምሪያው ሁሉም ሰራተኞች ከስራ ቦታቸው በሰዓቱ ተገኝተው አገልግሎት እንዲሰጡ የክትትልና የቁጥጥር ስራ እየተሰራ ነው፡፡ ችግር ያለበት ባለሙያና ቡድን መሪ ካለ በመማማሪያ መድረክ እና በማኔጅመንት ኮሚቴ እየተገመገመ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

ተገልጋይ ወደ ተቋማችን ሲመጣ ግልፅነት፣ ወጥነትና ተጠያቂነት ያለው አገልግሎት ማግኘት እንዳለበት ይታመናል፡፡ ነገር ግን አገልግሎት አሰጣጣችን ዘመናዊ ካለመሆኑ ጋር በተያያዘ የምንሰጣቸው አገልግሎትቶች ፈጣንና ግልፅ ላይሆኑ ይችላል፡፡ ይህ ሲባል ለስራው ጊዜ ሰጥቶ በትኩረት አይሰራም ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሁሉም የስራ ቀናት የስራ ድልድል ያላቸው ሲሆን ማክሰኞና ዓርብ በምክትል ስራ አስኪያጂ በኩል ሁሉንም ባለጉዳይ በጋራ አገልግሎት ይሰጣል፡፡ ሐሙስ ቀን ደግሞ የሳምንቱን የስራ እንቅስቃሴ ግልጽና ወጥነት ባለው አሰራር መፈጸም አለመፈጸማችን በጋራ ይገመገማል፡፡ ሰኞ ቀን ደግሞ መፈታት ያለባቸው ጉዳዮች በዋና ስራ አስኪያጂ በኩል ቀርበው ጉዳይ እንዲፈታ ይደረጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በየሳምንቱ ረቡዕ ቀን ደግሞ በከንቲባ ደረጃ በዋና ስራ አሲኪያጂ በኩል ያልተፈቱ ችግሮች ቀርበው ውሳኔ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

በእኔ በኩል ወደተቋማችን አገልግሎት ፈልጎ የሚመጣ ባለጉዳይ ተመሳሳይ ጉዳይ (መሬት ነክ) ይዞ ስለሚመጣ 10 ሰዎችን በአንድ ላይ በማስገባት ጉዳያቸውን በመግለጽ ችግራቸው እንዲፈታ ይደረጋል፡፡ ይህን አሰራር ተግባራዊ ማድረግ መቻሉ የጊዜ ብክነት እንዳይኖር ከማድረግ ባሻገር የእጅ መንሻ ለመስጠት የሚደረግን መደለያ ያስቀራል፡፡ ባለጉዳይን በጋራ ማስተናገድ መቻሉ ለደንበኞች የሚሰጠው መልስ ትክክለኛና ተገቢ መሆንና አለመሆኑን ሌሎችም መታዘብ ይችላሉ፡፡ ይህ መሆኑም በአጭር ጊዜ ብዙ ባለጉዳይ ማስተናገድ እንድንችል ያደርጋል፡፡ ይህ አሰራር በስራ አስኪያጂ

ደረጃ ሳሆን ባለሙያውና ቡድን መሪው ሁሉንም ባለጉዳይ በማስገባት ያስተናግዳሉ፡፡

ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት በአግባቡ መጠቀም አለመቻሉ በባለሙያውና በተገልጋዩ መካከል እጅ መንሻ የመስጠትና የመቀበል ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ አገልግሎት ለማግኘት ለመስጠት የሚደረግ የእጅ መንሻ(መደለያ) መስጠትንና መቀበልን ከማህበረሰቡ ጀምሮ እስከ አመራሩ ድረስ ሊፀየፈው ይገባል፡፡ አገልግሎት አሰጣጡን ለማሻሻል በቡድን መሪውና ለባለሙያው የተሰጣቸውን የስራ ድርሻ በአግባቡ ማከናወን ካልቻሉና በወቅቱ ካልፈፀሙ ሌላ ፍላጎት እንዳለ በመረዳት በጥብቅ በመከታተል የተጠያቂነት ስራ ይሰራል፡፡



በቅንነት ማገልገል ክብር ነዉ!!

በመምሪያችን በዋናነት የምንሰጣቸው አገልገሎቶች በጣም በርከት ያሉ ናቸው፡፡ ለአብነትም በማህበር፣ በሊዝ ጨረታ፣በምደባ(በውሳኔ)ለተፈቀደላቸው ግለሰቦች ካርታ መስራትና ቦታውን ለክቶ ማስረከብ፤ በልማት ምክንያት ከቦታቸው ለሚነሱ ባለመብቶች ደረጃ በደረጃ ውሳኔ እንዲያገኙ በማድረግ የትክ ቦታ ማዘጋጀትና ካርታ መስራት፣ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ለከንቲባ ኮሚቴ መላክ፣ የማስፋፊያ ቦታ የሚጠይቁ ባለሃብቶች መረጃውን በመመሪያው መሰረት አጣርቶ ለከንቲባ ኮሚቴ የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፣ ለተለያዩ የእምነት ተቋማት የአምልኮና የቀብር ቦታ ጥያቄን በመመሪያው መሰረት እንዲያሟሉ አድርጎ ለከንቲባ ኮሚቴ መላክ፣ በስማቸው ቤትና ቦታ ያለ(የሌለ) ስለመሆኑ ማስረጃ መስጠት፣የሊዝ ውል መያዝ፣ የመዋቅራዊ ፕላን መረጃ መስጠት፣የዘርፍ ለውጥ ጥያቄን መፍታትና የባንክ እና የፍርድ ቤት እግድ መስጠት የሚሉት በዋናነት ከምንሰጣቸው አገልግሎቶች መካከል ናቸው፡፡

አገልግሎት ፈልገው ወደተቋማችን የሚመጡ ባለጉዳዮች የተለያዩ ቅሬታዎችን ያነሳሉ፡፡ ማህበረሰቡም ወደ እኛ ተቋም ሲመጣ ቅሬታውን የት ቢሮ ማቅረብ እንዳለበት በአግባቡ ሳይረዳ ስለሚቀር ለተለያየ እንግልት ይዳረጋል፡፡ በዚህ መሰረት የግለሰቦች ቅሬታ ለመጓተቱ ምክንያት በባለሙያውና በአመራሩ እኔን አይመለከትም የሚል እሳቦት በመፈጠሩ በወቅቱ ቅሬታው መልስ ላያገኝ ይችላል፡፡ ነገር ግን በመምሪያ ይሁን በክፍለ ከተማ ደረጃ ተገቢ የሆኑ ጥያቄዎች መፈታትና ማለቅ ሲኖርባቸው ባለመሰራቱ ባለጉዳይ ቅሬታ ያቀርባል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ቅሬታ ሲገጠመን በቀጥታ በስልክ ወይም በአካል ጉዳዩን በመረዳት የእኛን እገዛ በመስጠት ቅሬታቸው እንዲፈታ እናደርጋልን፡፡

ይህን አሰራር በተጨባጭ ተግባራዊ እያደረግንበት ያለው አሰራር የስራ አሰኪያጂ ችሎት ነው፡፡ የስራ አስኪያጂ ችሎት በመምሪያ ደረጃ በስራ አሲኪያጂና በምክትል ስራ አሰኪያጂ የተወሰኑ ውሳኔዎች መፈጸምና አለመፈጸሙን የምናረጋግጥበት ነው፡፡ ይህ አሰራር ተጠያቂነትና ሃላፊነትን መውሰድን ሁሉ የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ለባለጉዳዩ ምላሽ መስጠት ያልቻለ አካል ለምን ምላሽ እንዳልሰጠ በባለጉዳዩ ፊት ተጠያቂ የሚሆንበት አሰራር የፈጠረ ነው፡፡

ስለዚህ በየደረጃው ያለውን ቅሬታ መፍታት ካልተቻለ ከላይ እንደተገለጸው ረቡዕ ዕለት በከንቲባ ችሎት ላይ በመገኘት ዋና ስራ አስኪያጂ ተጠያቂ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በከንቲባ ችሎት ላይ ተሳታፊ ከሚሆኑት ውስጥ ዋና ስራ አስኪያጁ፣ ምክትል ስራ አስኪያጁና ቡድን መሪዎች ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ያልተወሰነለት አካል ለምን እንዳልተፈፀመለት ስለሚጠየቅ ሁሉም አካል ከተጠያቂነት ራሱን ለማዳን ሲል ስራውን በአግባቡ ይወጣል፡፡ በጥቅሉ የሰራ አስኪያጂና የከንቲባ ችሎት የባለጉዳዩን ቅሬታ ለመፍታት ከፍተኛ የሆነ ድርሻ አለው፡፡ ለአብነትም በከንቲባ ችሎት ላይ 36 ዓመት የቆየ ቅሬታ መፍታት ሲቻል በስራ አስኪያጂ ችሎት ደግሞ 15 ዓመት የቆየ ቅሬታ ተፈቷል፡፡ ይህ ሲሆን ከክፈለ ከተማ

ጀምሮ እስከ ላይኛው ድረስ ድርሻው ከፍተኛ ነው፡፡

የመጣውን ቅሬታ በአግባቡና በወቅቱ መፍታት ባለመቻሉ በተጓተተ ቁጥር መመሪያዎች ይቀያየራሉ፡፡ ስለዚህ ባለጉዳዩን በአግባቡ ለማስተናገድ እንቸገራለን፡፡ ነገር ግን የሚመለከተው አካል አብሮ መወሰን ከቻለ ሁሉን ቅሬታዎች መፍታት ይቻላል፡፡ በየወቅቱ የአመራር መለዋወጥና የመመሪያ መቀያየር እኔን አይመለከተኝም በሚል እሳቤ ችግሮች እንዲራዘሙ ያደርጋል፡፡ አንዳንድ ጉዳዮች አሁንም በመመሪያ መቀያየር ምክንያት ረጅም አመት አስቆጥረው ያልተፈቱበት ምክንያት አለ፡፡ አሁን ያለው መመሪያ የመሬት ጉዳይ በክልል ደረጃ የሚፈታ ቢሆንም የተወሰኑ ስራዎችን በውክልና ለከተማ አስተዳደሩ ይሰጣል፡፡ ስለዚህ መመሪያው እኛን ቢከለክለንም ጉዳያቸውን በአግባቡ በመረዳት ግልፅ ደብዳቤ ለክልል በመፃፍ ቅሬታቸው እንዲፈታ እያደረግን ነው፡፡ በይዞታ ልኬታ የሚያጋጥሙ ጉዳዮች ሲኖሩ ደግሞ አጣሪና አፅዳቂ ኮሚቴ ያፀደቀውን ማንም መንካት ስለማይችል ጉዳዩ እንደገና እንዲታይ ይደረጋል፡፡ እኛ ይሄን ችግር መፍታት ስለማንችል ለክልል ቢሮ እንዲታይ ብለን በመፃፍ እነሱ እንዲጽፉልን በማድረግ ጉዳዩን ለመፍታት ተሞክሯል፡፡

አገልግሎት ፈላጊ ወደዚህ ተቋም ሲመጣ አገልገሎት ለማግኘት ህጋዊ መብቱን ተጠቅሞ ከማስፈፀም ይልቅ ተቋሙን ጥቅል በሆነ መንገድ የመፈረጅ ስራ ይሰራል፡፡ ስለሆነም ማህበረሰቡም ስራቸውን አክበረው ለሙያቸው ታምነው የሚሰሩ ሰዎችን በማበረታት ብልሹ አሰራርን በመታገልና መብቱን ማስከበር ይገበዋል፡፡ በዚህም መንገድ ባለጉዳዩ ችግር አለ ብሎ ቅሬታ ሲያቀርብ መታገል የሁሉም ባለሙያና አመራር ሊሆን ይገባል፡፡

በእኛ በኩል ችግሮችን ለመፍታት የመረጃ ዴስክ ባለሙያ በማቋቋም የሚመጣው ባለጉዳይ በቂ መረጃ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ ቢሮ ውስጥ በማንኖርበት ጊዜ ባለጉዳይ ያለአግባብ ጊዜውን እንዳያባክን መረጃ ማግኘት ያስፈለገዋል፡፡ ስለዚህ ከአሁን በፊት የነበረውን አሰራር ወደ ጎን በመተው ባለሙያ መድቦ የተስተካከለ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር በማድረግ አላስፈላጊ እንግልት ለማስቀረትም እየሰራን ነው፡፡ የሚመጣው ባለጉዳይ ይዞት የመጣውን ጉዳይ ለማን ማቅረብ እንዳለበት ጭምር የተሟላ መረጃ በማስፈር ባለሙያው ወደ እርሱ ምን ፈልጎ እንደመጣ ሁሉ የተሟላ መረጃ ለመስጠት ቀልጣፋ አሰራርን በመዘርጋት ላይ እንገኛለን፡፡

ስለዚህ ይህን ኋላ ቀር የሆነ አሰራር በዘመናዊ መረጃ ዴስክ ታግዞ ማንና ምን እንደሚፈልግ በመጠየቅ ማስተናገድ ይገባል፡፡ ይህን ለማከናወን የሁሉም አገልግሎት ሰጭ ባለሙያ የስራ ዝርዝር ሰጥተን ለተገልጋዩ ምቹና ቀልጣፋ አገልግሎት እንዲያገኝ ዝግጅታችን ጨርሰናል፡፡

አገልግሎት አሰጣጣችን ቀልጣፋ እንዳይሆን ያደረገው የመሬት ፋይል መረጃ ስርዓታችን ችግር መኖሩ ነው፡፡ ይህ ተግባር በሁሉም ክፍለ ከተማዎች በከፍተኛ ሁኔታ ይታያል ፡፡ ለአብነትም አንድ ክፍለ ከተማ ሄደን ምን ያክል ፋይል እንዳለ ብንጠይቅ ትክክለኛ ቁጥር ማግኘት አንችልም፡፡ ቁጥሩ በትክክል ካለመታወቁ ባለፈ የብዙ ሰዎች ፋይል ሆን ተብሎም ይሁን በትክክል በመጥፋቱ ምክንያት ለማሳወጅ ለከፍተኛ እንግልትና ለገንዘብ፣ ለጊዜና ለጉልበት ኪሳራ እየተዳረጉ ይገኛሉ፡፡ ይሁን እንጂ የተፈጠረው ችግር የሚጎዳው የእኛን አገልግሎትና አገልግሎት ፈላጊውን ነው፡፡ አንዳንድ ባለሙያዎች ይህን ሁኔታ እንደምቹ አጋጣሚ በመጠቀም ለመደራደር ይጠቀሙበታል፡፡ ይህን አሰራር መፍታት ካልተቻለ የከተማ የመሬት ጥያቄ መፍታትና ዘመናዊ ከተማ መገንባት አይቻልም፡፡

ብልሹ አሰራርን ለማስተካከል፣ የተደራጀ፣ ግልፅና ወጥነት ያለው አሰራር መስራት የሚቻለው በቴክኖሎጂ የተደገፈ ስርዓት ማልማት ሲቻል ነው፡፡ ስለዚህ ችግሩን ለመፍታት ከባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የመረጃ ስርዓት በማበልጸግ በሁሉም ክፍለ ከተሞች ከሰኔ 2016 ዓ.ም ጀምሮ የሙከራ ስራ ተግባራዊ በማድረግ ላይ ነን፡፡ ይህን ስራ ለማስኬድ ስድስት ሚሊዮን ብር በመበጀት የስራ መሳሪያዎች በማሟላት እና የአይሲቲ ባለሙያዎችን በመቅጠር ስራ አስጀምረናል፡፡ ከእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ የሚሰራውን ስራ በሰርበር አማካኝነት በማገናኘት የእያንዳንዱን እንቅስቃሴ መከታተልና መቆጣጠር የምንችልበት አሰራር ዘርግተናል፡፡ ይህ አሰራር የግለሰቡን ሙሉ ፋይልና ግብር የከፈለበትን ደረሰኝ ጨምሮ ሌሎች መረጃወችን ስካን በማድረግ ገቢ ይደረጋል፡፡ በየቀኑም ምን ያክል ፋይል ወደ ዘመናዊ የመረጃ ስርዓት እንደገባ በአይሲቲ ባለሙያው አማካኝነት እንከታተላለን፡፡ ባለፉት ሶስት ወራት በዚህ የመረጃ ስርዓት ውስጥ ከ20 ሺህ በላይ መረጃዎችን ገቢ ማድረግ ተችሏል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም በእቅድ ደረጃ የያዝነው በጂአይኤስ በመታገዝ የመሬቱን ድርሻ ከፋይሉ ጋር ማያያዝ ነው፡፡ ሙሉ መረጃውን ሲስተም ላይ በማስገባት የት ቦታ እና አካባቢ እንዳለ ማየትና መቆጣጠር እንችላለን፡፡ በዚህ መሰረት ጥርት ያለ የመረጃ አያያዝ ስርዓት በማበልፀግ እና አሰራርን በማዘመን ውስን የሆነውን የመሬት




**ደንበኛ የሁልም ነገር ምንጭ ነው!!**

ሃበት ከደላሎችና ያላአግባብ መጠቀም ከሚፈልጉ ሰዎች ነፃ ማድረግ ይቻላል፡፡ በዚህ የመረጃ ስርዓት ውስጥ ያለፈን መሬት ማንም ሰው እንደፈለገ ማስፋትና መውሰድ ስለማይችል ፍትሃዊ አሰራር እንድንከተል ያደርጋል፡፡

በመሬት መረጃ ስርዓት ፋይል ውስጥ የገባን መረጃ ከተፈቀደለት ባለሙያ ውጭ ማስተካከል ስለማይቻል ከብልሹ አሰራር የፀዳ እንዲሆን ያስችላል፡፡ ነገር ግን ይህ አሰራር ወደ ተግባር እንዳይገባ ከታች ከደላላው ጀምሮ እስከ ከፍተኛ አመራሩ ድረስ መቃወምና መተቸት ይሰተዋላል፡፡ ስለዚህ ከእንደዚህ ዓይነት እሳቤ ወጥቶ ሁሉም ባለ ድርሻ አካላት ድጋፍና ክትትል በማድረግ ዘመናዊነትን የሚያሳድግ እና እንግልትን የሚያስቀር አሰራር ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ዘመናዊ አሰራር ተግባራዊ ካልተደረገ አመራሩ በተቀያየረ ቁጥር የችግሩ ገፈት ቀማሽ ባለጉዳዩ ነው፡፡

ሌላው ብልሹ ሰራርንና የደንበኞችን እንግልትን ለመቀነስ ታሳቢ ያደረገ ከስራ አስኪያጅ ቢሮ ጀምሮ እስከ ባለሙያው ድረስ ካሜራ ለመግጠም ስራዎችን አጠናቀናል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ በደንበኞችና በባለሙያው መካከል የሚደረጉ ያልተገባ ግንኙነትን ያስቀራል፡፡ የሰራ ሰዓታቸውን በማክበር ከስራ ቦታቸው በመገኘት አገልግሎት እንዲሰጡ ያስገድዳል፡፡ በመምሪያ ደረጃ የታቀደው የካሜራ ገጠማ ስራ በክፍለ ከተሞችም ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

በመጨረሻም አቶ ወንዳለ በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ለብልሹ አሰራር የተጋለጡ ባለሙያዎች (አካላት) እሳቸው ወደ ተቋሙ ከመጡበት ጊዜ ጀምሮ ያላጋጠማቸው ቢሆንም ከዚህ በፊት ብልሹ አሰራር የፈፀሙ ባለሙያዎች ህግና ስርዓት ለማስከበር መንግስት እርምጃ እንደወሰደ ገልፀው ጉዳያቸው በስነ ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን እና በፍርድ ቤት ደረጃ እየታየ እንዳለ በማረጋገጥ ባለሙያዎችና አመራሩ ከእንደዚህ አይነት ጥፋት ራሳቸውን እንዳያስገቡ በመማማሪያነት እንደ ሚጠቀሙበት እንዲሁም ከአሰራር ውጭ ሲንቀሳቀስና ብልሹ አሰራርን የሚተገብሩ አካላት ካሉ የማያዳግም የእርምት ርምጃ እንደሚወስዱ ሃሳባቸውን ገልፀዋል፡፡

አቶ ወንወዳለ ይህን ይበሉ እንጂ የሐዲስ መጽሔት ዝግጅት ክፍል መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ተቋሙ በተንቀሳቀስንበት ወቅት ያነጋገርናቸው ባለ ጉዳዮች ያነሷቸው ችግሮች እኛም በቦታው ተገኝተን ያረጋገጥናቸው ናቸው፡፡ ዝግጅት ክፍሉም በቦታው 9፡00 ሰዓት ላይ በደረስንበት ወቅት ቢሮው ባለጉዳይ የሚስተናገድበት አይመስልም ነበር፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ወረፋ ለመያዝ የሚመጡ ባለጉዳዮች በደንብ አስከባሪዎች ሲንገላቱና ሲመናጨቁ ከማየት ባለፈ የሚፈለገው አመራር ወይም ቡድን መሪ ቢሮ እንደሚገባ እና እንደማይገባ መረጃ የሚሰጥ አካል አለመኖሩ የተቋሙ አሰራር በእጅጉ መሻሻል እንደሚገባው አመላካች ነው፡፡ በተቋሙ በኩል በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተደግፎ ለመስራት ያሉ መልካም የአሰራር ጅማሮዎችን አጠናክሮ በማስቀጠል ብልሹ አሰራርን መታገል ከሁሉም ባለድርሻ አካላት የሚጠበቅ መሆኑን በመገንዘብ አስፈላጊውን መረጃ በወቅቱ መስጠትም ሆነ ማስተናገድ እንደነውር የሚቆጠርበት ሁኔታ ስላለ የሚመለከተው አካል ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለበት ዝግጅት ክፍሉ መልዕክቱን እያስተላለፈ የዛሬውን በዚህ አጠናቀናል፡፡ ሰላም!!

# የፀና የትውልድ ውርስ

በይበልጣል መኮንን

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የብዝኃ-ሕይወት ኃብት ካላቸው አገራት መካከል አንዷ ናት፡፡ ብዝኃ -ሕይወት ስንል ሁሉንም ሥነ-ሕይወታዊ ኃብቶች ማለትም እፅዋትን ፣ እንስሳትን ፣ ደቂቅ ዘአካላትን እና በውስጣቸው የያዟቸውን ዘረ-መሎች አካቶ የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ኃብቶች ለአካባቢው ጤናማነትም ሆነ ለሰው ልጅ ኑሮ እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ መሆናቸው የሚታመንባቸው ናቸው፡፡

ይሁን እንጅ የሰው ልጅ ብዝኃ-ሕይዎትን እያመናመነ እና አካባቢውን እያዛባ ይገኛል፡፡ ከትውልድ-ትውልድ የዕጽዋት መመናመን፣ የደን ሽፋን መራቆት እና የአካባቢ መበከል ተዳምሮ የአየር ንብረት ቀውስ ተጠናክሮ እንዲቀጥል አስችሎታል። በዚህ ሳቢያ የተከሰተው የአየር ንብረት ለውጥ የዓለም ሙቀት በአደገኛ ሁኔታ እንዲጨምር አደረገ፡፡ ይህ ሁሉ ተግዳሮት ተዳምሮ የዓለምን ሕዝብ የቀውስ አዙሪት ውስጥ ጨምሮታል፡፡

በደን መመናመን እና በአለም ሙቀት መጨመር ሳቢያ የበዛ የተፈጥሮ አደጋ ፣ ታይቶ የማይታወቅ ከፍተኛ ሙቀት ፣ የተጠናከረ ሰደድ እሳት ፣ ከፍተኛ ዝናብና ጎርፍ እንዲሁም ጠንካራ ማዕበልና ውሽንፍር እየደረሰ ያለው ጉዳት ከመጠን ባለፈ እየጨመረ ለዓለም ሕዝብ ፈተና ሆነ፡፡ ፈተናው በተለይም ኢኮኖሚያቸው ግብርናው ላይ መሰረት ያደረጉ ሀገሮችን በእጅጉ ጉድቷል፡፡ የአየር ንብረት ተፅኖ ሊቀለበስ ከማይችልበት ደረጃ ላይ መድረሱን በዓለም ደረጃ ያሉ የአየር ንብረት ለውጥን የሚከታተሉ አካላት ጥሪያቸውን በተደጋጋሚ ሲያሰሙ መስማት የተለመደ ሆኗል፡፡

በዚህ ረገድ የዓለም ስጋት የሆነው የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት ፣ የምድር መጎሳቆል ፣ የዕጽዋት መመናመን ጉዳይ ቀድመው የተረዱ እና የችግሩ ጥልቀት ያስጨነቃቸው ሀገራትና ተቋማት በየፊናቸው አመርቂ ተግባራትን ሲያከናውኑ ይስተዋላል፡፡ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር ተያይዞ ለተከሰተው ችግር መፍትሄ ከተቀመጡ የፖሊሲ አቅጣጫወች መካከል አንዱ ሀገራት የደን መመናመንን በማስቀረት ፣ ቀጣይነት ያለውና መጠነ-ሰፊ የደን ተከላ እና እንክብካቤ ስራ መስራት ፣ ከአየር ንብረት ጋር የተጣጣመ ግብርናን በመተግበር እና የሙቀት አማቂ ጋዞች ልቀትን መቀነስ እንደሚገባ የጋራ ግንዛቤ ተይዞ ሲሰራበት ቆይቷል፡፡

እንደ ሀገር የአየር ንብረት ቀውስ ከሰብዓዊ ህይወት ጋር ያለውን ቁርኝት ቀድማ የተረዳችው ሀገራችን ኢትዮጵያ እየገጠማት ያለውን ችግር ለመቋቋምም ሆነ የዓለም ሀገራትን ጥሪ ተቀብላ ለአየር ንብረት ለውጥ ምላሽ ለመስጠት አይነተኛ መፍትሄ ነው ያለችውን የአርንጓዴ አሻራ ልማትን ዘርግታለች፡፡ በተዘረጋው የአረንጓዴ አሻራ ልማት መርሐ-ግብር ኢትዮጵያ እያስመዘገበችው ያለው አመርቂ ለውጥ የዓለምን ትኩረት መሳብ ችሏል፡፡

ጥንትም ቢሆን የኢትዮጵያ የታሪክ መዛግብት እና ድርሳናት የሚናገሩት የደን ሃብትን በማልማት ፣ በመንከባከብና በመቆጣጠር ዙሪያ የኢትዮጵያ ነገስታትና መንግስታት የተለያዩ ጥረቶችን ያደርጉ እንደነበር ያትታል፡፡ ይህ አድራጎታቸው ሀገራችን ኢትዮጵያን በደን ሃብቷ ከአፍሪካ ሀገራት ግንባር ቀደም አድርጓት ቆይቶ ነበር፡፡ ይሁን እንጅ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመጣው የሀገራችን የህዝብ ብዛት የእርሻና የግጦሽ መሬት እጥረት የደን ሃብት ያለመሰሰት ተጨፈጨፈ፡፡ ይህ እኩይ ተግባር የኢትዮጵያ ሕዝብ በተደጋጋሚ ለአየር ንብረት ለውጥና ለተፈጥሮ አደጋ ተጋላጭ እንዲሆን አድርጉታል፡፡

በዚህ ሳቢያ የሀገራችን የደን ልማት ሌጋሲ በማስቀጠል ረገድም ይሁን የተፈጥሮ ሚዛን መዛባት በእጅጉ ያሳሳበቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ ችግሩን ለመቅረፍ በቁርጠኝነት የሚተገበር የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ፕሮጀክትን ከጥቂት ዓመታት በፊት ይፋ አደረጉ፡፡ በጠቅላይ ሚንስትሩ አነሳሽነት የተጀመረው ይህ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ- ግብር ፕሮጀክት በአሁኑ ሰዓት ከፍተኛ የሆነ ለውጥ እና ተቀባይነትን እያገኘ መጥቷል፡፡

ቀጣይነት ባለው መልኩ የሚተገበረው ይህ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ወደ ሌሎች ጉረቤት ሀገሮችም እንዲዛመት የማድረጉ ሂደት እንዲሁ በቀጠናው በፍጥነት ተቀባይነትን አግኝቷል፡፡ ይህ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለጉረቤት ሀገሮች ችግኝ ሰጥተው እንዲተክሉ የማድረጋቸው ጅማሮ የአረንጓዴ አሻራ ልማት መርሐ- ግበር በቀጠናው እንዲስፋፋ በር የከፈተ ሰናይ ተግባር አሰኝቷል፡፡ ኢትዮጵያ የዘረጋችው የአረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክት የአየር ንብረት ለውጥን ተቋቁሞ የህዝቡን ኑሮ በመለወጥ እረገድ ትልቅ ፋይዳ እያስገኘ በመምጣቱ የመጭው ትውልድ ውርስ ተደርጎ በቋሚነት መሰራት እንዳለበት በስፋት ይነገራል፡፡

ይህን የትውልድ ውርስ የአረንጓዴ አሻራ ፕሮጀክት አስቀጥሎ እንዲሻገር ከማድረግ አንፃር የአማራ ክልል እንዴት እየተገበረው ነው ፣ የመርሐ-ግብሩ አሁናዊ ሁኔታውስ ምን ይመስላል እንዲሁም ምን ተሰራ ምን

ጎደለ የሚሉትንና ሌሎች መሰል ጥያቄዎችን አንስታ ሐዲስ መጽሔት በዘርፉ የሚመለከታቸውን እንግዳ አነጋግራ እንካችሁ ትላለች መልካም ቆይታ፡፡

አቶ እስመለዓለም ምሕረቱ በአማራ ክልል ግብርና ቢሮ የክልሉ የተፈጥሮ ሀብት ልማት ጥበቃና አጠቃቀም ዳይሬክቱሬት ዳይሬክተር ናቸው፡፡ ዳይሬክተሩ እንደሚሉት የአረንጓዴ አሻራ ልማት መርሐ-ግብር ከመጀመሩ በፊት የክልሉን የደን ልማት ሽፋን ወደ ተሻለ ደረጃ ለማምጣት ቀድሞም ይሰራ ነበር፡፡ ይህም ሆኖ የክልሉ የደን የመፅደቅ ምጣኔ እየቀነሰ መምጣቱን የሚያሳይ ነው፡፡ ችግሩን ለመለየት በ2009 እና በ2010 ዓ.ም የተለያዩ ጥናቶች ተጠንተዋል፡፡ የጥናቶች ውጤት እንደሚያመለክተው በክልሉ የሚታቀዱ እቅዶች በአብዛኛው ከላይ ወደታች የወረዱ መሆናቸው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ህብረተሰቡ በሚፈልገው ልክ ስለማይታቀድ እና አካባቢውን መሰረት ያደረገ ባለመሆኑ የተተከሉ የችግኞች የመፅደቅ ምጣኔያቸው እየቀነሰ መጥቷል የሚል ድምዳሜ ላይ ለመድረስ አስችሎናል፡፡

በጥናቱ መሰረት እቅዱ ከተች ወደ ላይ ሲታቀድ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ችግኞችን የሚተክለው ማን ነው? የሚተከሉት ችግኝ ምን አይነት ናቸው? የሚተከሉትስ የት ቦታ ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች ምላሽ በሚሰጥ መልኩ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ በዚህ ሁኔታ የክልሉን የደንሽፋን ለማሻሻል ሲሰራበት ቆይቶ በ2011 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ተጀመረ፡፡ ይህ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር መጀመሩ የነበረውን የክልሉን የደን ልማት አጠናክሮ ለመስራት ጥሩ ግባት ሆኗል፡፡

“ሰውና ተፈጥሮ የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፡፡” ሰውና



“አንድም ችግኝ ባለቤት ሳይኖረው አይተከል”
አቶ እስመለዓለም ምሕረቱ

ተፈጥሮ ተጣጥመው ይኖሩ ዘንድ የደን ልማት ስራው በእጅጉ አስፈላጊ ነው፡፡ የዚህ የአረንጓዴ አሻራ ትግበራ ዋና ዓላማም ይህን የሚያፀና ነው፡፡ የደን ሽፋንን ከፍ ማድረግ እና እየተዛባ የመጣውን የአየር ንብረት ለውጥ አስተካክሎ የአግሮ-ኢኮሎጅ ቀጠናውን ማሻሻል ላይ አልሞ የሚሰራ ሲሆን የአየር ንብረት ለውጥን ተዋግቶ ቀጣይነት ያለው ልማት ማስፋፋት ብሎም ሀገራችን በዓለም አቀፍ ደረጃ ይበልጥ እንድትታወቅ ማድረግ ላይ ያተኩራል፡፡ ከዚህ አኳያ የሀገራችን ገጽታ ከመገንባት አንጻር የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በዚህ እረግድ አግሮኢኮሎጅውን ጠብቆ ቱሪዝሙን ማሳደግ ነው፡፡

በአለፉት ዓመታት በአረንጓዴ አሻራ ልማት መርሐ-ግብር በተሰሩ ስራዎች የክልሉ የደን ሽፋን ከነበረው 14 በመቶ ወደ 16 ነጥብ ሶስት በመቶ ማሳደግ ተችሏል፡፡ እስካሁን ባለው ሁኔታም ስምንት ነጥብ ሶስት ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ሲቻል በሄክታር ከ400 ሽህ በላይ መሸፈን ተችሏል፡፡ ትግበራው በአስር ዓመቱ እቅድ መጨረሻም 22 በመቶ ለማድረስ ታቅዶ እየተሰራ ነው፡፡

እንደክልል በአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ከተከናወኑት ተግባራት መካከል የቦታ ልየታና መረጣ በዋናነት በግንባር-ቀደም ሊጠቀስ የሚችል ተግባር ነው፡፡ ችግኞችን ለማፍላትም ሆነ ለመትከል የቦታ መረጣ እና ልየታ ስራ ተቀዳሚ ተግባር ነው፡፡ ይህም በየአካባቢው የአፈር አይነት እና

# ልማት/ኢኮኖሚ

አግሮኢኮሎጅ ቀጠናው እየተለየ የሚሰራ ነው፡፡ በዚህ መለኪያ ቦታው ከተመረጠና ከተለየ በኃላ አብሮ የሚመጣው ተግባር ባለቤቱ ማነው የሚለው ጉዳይ ነው፡፡

ሁሉም ችግኞች ሲተከሉ ባለቤት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ "አንድም ችግኝ ባለቤት ሳይኖረው አይተክል፡፡" ችግኞች ባለቤት ሲኖራቸው ባለቤቱ የሚተክለውን ችግኝ ለይቶ በማወቅ ይንከባከባል፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ችግኙን የሚያፈላ ፣ የሚተክል እና የሚንከባከበው የራሱ የሆነ ባለቤት ሲኖረው የፅድቀት ምጣኔው በዛው ልክ ይጨምራል፡፡ በዚህ መጠን ስራዎች ሳይንሳዊ ዘዴያቸውን ተላብሰው የባለቤትነት መንፈስም ታክሎበት ፣ ፍትሀዊ ተጠቃሚነትንና ዘላቂነትን በሚያመጣ መንገድ ችግኞችን የማፍላት ፣ የመትከልና የመንከባከብ ተግባር እየተሰራ ነው፡፡ ጥራት ያለው የአረንጓዴ አሻራ ልማትን ለመተግበር ከተፈለገ ዓላማውን መሰረት ያደረገ የቅድመና የድህረ ተከላ የችግኞች አያያዝና እንክብካቤ ስራወች ምን መምሰል እንዳለባቸው ቀድሞ መወሰን ያስፈልጋል፡፡

ለዚህ ደግሞ የህብረተሰቡ ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ ችግኝ ባልተተከለበት ቦታ እንዲተክል እና ችግኝ በተተከለበት ቦታ ደግሞ የምንከባከብ ስራ መስራት ነው፡፡ አሁን ባለው ደረጃ የህብረተሰቡ የአርንጓዴ አሻራ ስሜትና ተሳትፎ እያደገ መጥቷል፡፡ ይህንንም ከሚያደርገው ተግባር ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ሕብረተሰቡ በራሱ ገንዘብ ችግኝ ገዝቶ ፣ የመትከልና የመከባከብ ስሜቱ አድጓል፡፡ ይህ እንዲሆን ደግሞ እንደክልል ሕብረተሰቡ ባለቤቱ እኔነኝ ከሚለው እሳቤ እንዲደርስ ታስቦ በመሰራቱ የመጣ ውጤት ነው፡፡ለተተከሉት ችግኞች እየተደረገ ያለውን እንክብካቤ በተመለከተ ችግኞች በአንድ ቀን ደርሰው ባንድ ቀን የሚተከሉ አይደሉም፡፡ ጊዜን ፣ ጉልበትንና ሀብትን ይጠይቃሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ ሁሉ ነገር በተጠና መልኩ ሳይንሱ በሚያዘው ልክ ተግባራት እየተከናወኑ ናቸው፡፡ ያለው ሁኔታም የአረንጓዴ አሻራ ስራው በመንግስት ከፍተኛ አመራሮች ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ ፣ የቅድመ እና ድህረ-ተከላ ስራወች በየደረጃው በተቋቋሙ አቢይ ኮሚቴና የቴክኒካል ኮሚቴ በቋሚነት እንዲመራ ተደርጎ የእንክብካቤ ስራው ቀጣይነት ባለው መልኩ በእቅድ እየተመራ እየተተገበረ ነው፡፡

ሌላው ሲሰራበት የቆየው ተግባር ደግሞ የችግኞች የመፅደቅ ምጣኔ ለመጨመር የተከናወነው ተግባር ነው፡፡ በዚህ ተግባር በርካታ ስራዎች በውስጡ መከናወን ችለዋል፡፡ የችግኞች የመፅደቅ ምጣኔ ጥራት ካለው የዘር መረጣ ይጀምራል፡፡ ሳይንሳዊ የዘር አፈላል ስልቶችን ተከትሎ ችግኞች አግባብነት ያለው የጊዜ ቆይታ ሲደረግላቸው ፣ የመትከያ ጉድጓድ ስፋትና ጥልቀት ፣ በተከላ ወቅት የሚደረጉ ጥንቃቄዎች ፣ የአረምና የኩትኳቶ ስራዎችን ጨምሮ ለተከታታይ ሁለት ዓመታት የሚደረጉ የቅድመ እና የድህረ ተከላ ስራዎች ላይ መሰረት ተደርጎ ሲሰራ ነው፡፡ በዚህ መልክ በተደረገ ክትትል እንደክልል የመፅደቅ ምጣኔው ከባለፉት ዓመታት እየተሸሻለ መጥቶ 79 ነጥብ ስምንት ማድረስ ተችሏል፡፡ ለዚህ ደግሞ አሁን ላይ እንደ ክልሉ ሁኔታ ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚተከሉ ተለይተዋል፡፡ ለአብነት በደጋማው አካባቢ የተለያዩ ዝርያዎችን የማቅረብ ችግር ቢኖርም ከሚሰጡት ዘርፈ ብዙ ጥቅም የተነሳ ዲከረንስ (የተለያዩ የግራር ዝርያዎችን) ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚተከሉ ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በጣም በተራቆተ ፣ በተጋጋጠ እና ቀይ አፈር በበዛበት አካባቢ ራሱን ተቋቁሞ መሬቱን ሊያድን የሚችል የግራቪሊ ችግኝ ትኩረት ተሰጥቶት እተተከለ ነው፡፡ አሁን ላይ አንዳንድ አካባቢዎች ፍራፍሬን ትኩረት አድርገው እየሰሩ ነው፡፡ ለአብነት ዳንግላ እና ደቡብ አቸፈር ዙሪያ ቀደም ሲል ባህር-ዛፍ ይበዛበት የነበር እና አሁን ላይ በምትኩ የተለያዩ የፍራፍሬ ዝርያዎችን አትክለው ለውጭ ገበያ እያቀረቡ ነው፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች በርካታ ወጣቶችና አርሶ-አደሮች ተሞክሮውን እያዩ ዘርፉን ሲቀላቀሉ ማየት የተለመደ ነው፡፡ በተመሳሳይ ተራራማ በበዛበት አካባቢ ደግሞ አግሮኢኮሎጅውን ሊቋቋም የሚችለውን የባህር-ዛፍ ችግኝ እየተተከለ ይገኛል፡፡

ቀደም ሲል የደን ልማቱ ከመቀነሱ የተነሳ ምርትና ምርታማነትም ወርዷል፡፡ የእንስሳት ሀብት ፣ የከርሰ-ምድር ውሃ የፍራፍሬ እና መሰል ተፈጥሮን ጥገኛ ያደረጉ ምርቶች ቀንሰዋል፡፡ የዚህ ፍቱን መድሃኒት የሆነው የአረንጓዴ አሻራ ትግበራ ስራ መሬቱ እንዲድን አካባቢው በዛፍ እንዲሞላ ፣ ዝናብ በበቂ መጠን እንዲዘንብ ፣ በርሃማነት እንዲቀንስ ማስቻሉ ለአርሶ-አደሩ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮለታል፡፡

የተፈጥሮ ሀብታችንን መጠበቅ የኢኮኖሚያችን መሠረት ነው፡፡ የክልላችን ተፋሰሶችን በአግባቡ ከያዝን የክልሉ የውሃ ሃብት ይጨምራል። ውሃ ተገኘ ማለት ደግሞ ሁሉንም ነገር በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል ነው፡፡ በዚህ ልክ የውሃ መገኘት የኤሌክትሪክ ኃይል ለመገኘት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል። ስለዚህ ኃይል የሚገኘው ከውሃ ነውና የችግኞች መተከልና ውጤታማ መሆን ትልቁ ቁልፍ ጉዳይ ተደርጎ መወሰድ ያለበት ነው፡፡ በዚህ እረገድ የአማራ ክልል ለታላቁ የአባይ ግድብ አጎራባች ከመሆኑ የተነሳ ይህ የክልሉ የአረንጓዴ አሻራ ትግበራ አሁን ላይ ግድቡ ከፍተኛ የሆነ የውሃ ኃይል እንዲያገኝ

# ልማት/ኢኮኖሚ



የዲከረንሲ ግራር ዛፍ ልማት (አዊ ብ/እተዳደር)



የአረንጓዴ አሻራ (አረጎባ ወረዳ )

በማድረግ በኩል ከፍተኛውን አስተዋፅኦ እያበረከተ ነው፡፡ በዚህ ልክ ግድቡ በቂ ውሃ አገኘ ማለት ደግሞ ግድቡን በተያዘለት ሰዓት መሙላት ስለሚቻል ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ የሚያመጣው ፋይዳ ላቅ ያለ ነው።

አሁን ላይ የአረንጓዴ አሻራ ትግበራው ለክልሉ ሕዝብ ከፍተኛ የሆነ ጥቅም እያስገኘ ነው፡፡ የደኑ የሽፋን መጠን እያደገ በመምጣቱ ምክንያት የክልሉ የብዘሀ-ህይወት ሀብት በቁጥር ፣ በመጠንና በአይነት እየጨመረ መጥቷል፡፡ በቂ የሆነ የደን ሽፋን ሲኖር ወቅቱን የጠበቀ የዝናብ ፍሰት እንዲኖር ያስችላል፡፡ ወቅቱን የጠበቀ የዝናብ ፍሰት ኖረ ማለት ደግሞ አርሶ-አደሩ ወቅቱን ጠብቆ እንዲያመርትና ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ያደርጋል፡፡ የአፈር መከላት በእጅጉ ቀንሷል ከአሁን በፊት በደለል ይሞሉ የነበሩ አሁን ላይ መጠኑ ያነሰ ነው፡፡ ይህ ሲሆን የአፈር ለምነት ስለሚጠበቅ እንደሀገር የተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ለክልላችን ብሎም ለሀገር እያስገኘ ያለውን ዘርፈ ብዙ ጥቅም ጎልቶ እንዲታይ ያድርገዋል፡፡

ሌላው ደግሞ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ መገንባት መቻሉ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በዋናነት የክልሉን ኢኮኖሚ ለመደገፍ ትኩረት ሰጥቶ የሚተገበር ሲሆን በተለይም በግብርና እና በእንጨት ኢንዱስትሪ ውስጥ ብዙ የስራ እድል እንዲፈጠር አስችሏል። አሁንም ከወዲሁ የእንስሳት መኖ እና የፍራፍሬ ችግኞች ተተክለው በአጭር ጊዜ የሚታይ ጥቅም እየሰጡ ይገኛሉ። አቮካዶ ፣ ሌሎች ፍራፍሬዎች እና ንብ ማነብን ጨምሮ እየተገኙ ያሉ ጥቅሞች የክልሉን ሕዝብ ኢኮኖሚ በእጅጉ እየደገፉ ነው፡፡

የክልላችን የአረንጋዴ አሻራ ትግበራ ስራ እያስገኘ ያለውን ጥቅም በክልላችን ስር ባሉ ወረዳዎች የመጣውን ለውጥ በስፋት ማስተዋል ይቻላል፡፡ የኮንስትራክሽኑ እና ኢንዱስትሪው ዘርፍ እንዲሰፋ ከማድረግ አልፎ በደን ዘርፉ በተሰሩ ስራዎች ክልሉ ከደን ሴክተር የሚያገኘው ገቢ ከአመት አመት እየጨመረ ነው፡፡ የምርት እጥረቱን ችግር ከወዲሁ መቅረፍ እያስቻለ ነው። ለዚሁ ማሳያ በክልሉ ባሉ በተለያዩ ዞኖች ያለውን አጣና ምርት ማየት በቂ ነው፡፡ ይህ እንዲሆን እንደክልል እየተተከሉ ያሉት ችግኞች ኢኮኖሚያዊ ፋይዳቸው ላቅ ያለ አበርክቶት እንዲኖራቸው ታስቦ በመሰራቱ የመጣ ለውጥ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

ከስራ ዕድል ፈጠራ አንፃር የደን ዘርፉ ትልቅ አቅም እየፈጠረ ነው፡፡ በክልሉ ግብርና ቢሮ በኩል ይህን ዕድል ለመጠቀም በርካታ ወጣቶችን በደን ዘር ማሰብሰብ ፣ በችግኝ ማፍላት ፣ በአጣና ምርት ፣ ከሰል እና ሌሎች የደን ውጤቶች እንዲሰማሩ በማድረግ ለወጣቶቹ የስራ ዕድል በመፍጠር የክልሉን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ለማነቃቃት ጥረት እየተደረገ ነው፡፡ በዚህ እረገድ ለበርካታ የክልሉ ወጣቶች የስራ እድል

ተፈጥሮላቸዋል፡፡ ዘር ለቅመው እንዲሸጡ ፣ ችግኝ አፍልተው ለራሳቸው እንዲተክሉ ፣ በማድረግና ችግኝ አፍልተው እንዲሸጡ በማድረግ ራሳቸውን እና ቤተሰቦቻቸውን መደገፍ እየቻሉ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ በክልሉ በየአመቱ ከ270 እስከ ሶስት መቶ ሽህ የሚደርሱ ወጣቶች የሰራ እድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

እንደ አቶ እስመለዓለም ገለፃ የክልሉን የአረንጓዴ አሻራ ትግበራ ቅንጅታዊ አሰራሩ የተሄደበትን እርቀትና የተገኙ ውጤቶችን አስመልክቶ መላው የክልላችን የማህበረሰብ ክፍል ፣ አመራሩ ፣ ባለሙያው ፣ አርሶአደሩ ፣ የትምህርት ማህበረሰቡ ፣ የሚዲያ እና የጥበብ አካላት ፣ የሀይማኖት መሪወች ፣ የግል ባለሀብቱ ፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማትና የሲቪክ ማህበራትን ጨምሮ ሌሎችም በንቃት እንዲሳተፉ ልዩ ዕድል ተፈጥሮላቸዋል፡፡

በዚህ እረገድ ሴክተር ቢሮዎች የተከላ ቦታ በመረከብና ሙሉ ወጭውን በመቻል ተከላ እና የእንክብካቤ ስራ ማከናወናቸው ፣ ነጋዴዎችና ባለሀብቶች መኪኖቻቸውን ለተከላ ለሚውለው ህዝብ ማመላለሻ መስጠታቸው እና የተለያዩ ባለሃብቶች የራሳቸው የተከላ ቦታ ወሰደው በድርጅታቸው ስም ከተከላ ጀምሮ እስከ እንክብካቤው ድረስ በመስራት የቀጣይ የደን ልማቱን ስራ ዘላቂ ለማድረግ የነበሩ ቅንጅታዊ ስራዎች አበረታች ናቸው፡፡ ቅንጅታዊ ስራዎቹ ወጤታማ እንዴሆኑ ሰነዶች ተዘጋጅተው ከአጋር አካላት ጋር ቀድመው ውይይት እየተደረገባቸው ተገምግመው እንዲውርዱ መደረጉ ውጤት አምጥቷል፡፡

የክልሉን የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር ትግበራ ላይ ከሚያጋጥሙ ችግሮች አንዱና እስካሁንም ድረስ መፈታት ያልተቻለው የበጀት ጉዳይ ነው፡፡ የደን ስራ ከፍተኛ የሆነ ሀብትን የሚጠይቅ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ነገር ግን የደን ልማቱን በሚገባው ልክ እንዳይተገበር ማነቆ ሆኗል፡፡ ለዚህ ደግሞ ለደን ሀብት ልማት እየተመደበ ያለው አነስተኛ በጀት በዋናነት ይጠቀሳል የሚሉት ዳይሬክተሩ ዛሬ ለሚፈለው ችግኝ በጀት ከሌለው በ2020 ዓ.ም የደን ሽፋናችን መጠን በሚፈለገው ልክ ሊሄድ አይችልም፡፡

በመጨረሻም ዳይሬክተሩ የክልሉ ግብርና ቢሮ በደን ልማት ዙሪያ የሚሰራቸውን ስራዎች በትክክለኛው መንገድ በመከወን ክልሉን ብሎም ሀገርን በሚያሻግር መልኩ አስቦ መሰራት አለበት፡፡ ለዚህ ደግሞ ቢሮው ዘሮችን ከመምረጥ ጀምሮ ሳይንሳዊ የተከላ እና የምርምር ስራዎችን አጠናክሮ ማስቀጠል ተገቢ ነው፡፡ ባለሙያዎች በተሰጣቸው ኃላፊነት ልክ የሚፈሉ እና የሚተከሉ ችግኞችን የመቆጣጠርና የመንከባከብ ስራዎች ላይ አተኩረው መስራት ይኖርባቸዋል፡፡ ሕብረተሰቡም የተሰጠውን አደራና ምክር ተቀብሎ የእኔ ነው ብሎ ማልማት ይጠበቅበታል፡፡ በሌላ መልኩ የክልሉ አመራር በዘርፉ የሚከናወኑ ስራዎችን በትክክል መደገፍ ፣ መከታተል ፣ ስምሪት በመስጠት እና ለዘርፉ በቂ በጀት እንዲመደብ በማድረግ በኩል ከፍተኛ ጥረት ማድረግ አለበት፡፡ በተመሳሳይ ሚዲያው በቀጣይ ለሚተከሉ ችግኞች የቅስቀሳ እና የግንዛቤ ፈጠራ ስራ አስቀድሞ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ይህ ሲሆንና ሁላችንም የእኔ ነው ብለን የድርሻችን መወጣት ከቻልን ክልላችን በልማቱ ዘርፍ ተፅኖ ፈጣሪ ክልል ማድረግ እንችላለን በማለት ሀሳባቸውን አጠቃለዋል፡፡

የዝግጅት ክፍሉም አቶ እስመለዓለም ምሕረቱ ለሰጡን ማብራሪያ እና ምላሽ እያመሰገን ዕጽዋት በልምላሚያቸው ለምድር ጌጥ ብቻ ሳይሆኑ ለጤናማ ሕይወት እና ለተፈጥሮ ሚዛን መጠበቅ ዋስትና ናቸው፡፡ ዳሩ ግን የሰው ልጅ ብዝኃ-ሕይወትን እያመናመነ፣ አካባቢውን እያዛባ፣ ምድርን እያጎሳቁለ መሬት ለሰው ልጅ የምትሰጠውን ጤናማ ሕይወት ነጥቆ በአንገቱ ላይ ሸምቀቆ ሲያጠልቅ ይታያል፡፡ የሰው ልጅ በደን ሀብት ላይ እያደረሰ ያለው ዕኩይ ተግባር ሁሉ አሁን ለተፈጥሮ ሚዛን መዛባት ተጎጅውም ሆነ ተጠያቂው ራሱ የሰው ልጅ መሆኑን የዘነጋው ይመስላል፡፡

አለማችን እያስተናገደች ያለውን የአየር ንብረት ለውጥ በአይበገሬነት ለመቋቋም የምንችለውም ሆነ ከችግሩ የምንድነው የምንኖርበትን አካባቢ በአረንጓዴ እፅዋት ሽፍነን ለሰው ልጅ ምቹ፣ ውብና ማራኪ ለማድረግ ስንችል ነው፡፡ ይህ ሲሆን ደግሞ ከዘርፉ ኢኮኖሚያዊ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጠቀሜታውን ማረጋገጥ እንችላለን፡፡ የአየር ንብረት ቀውስን እና ተጽዕኖን ለመቋቋም የተፈጥሮ ኃብትን መጠበቅና መልሶ ደንን ማልማት አንዱ እና ብቸኛው አማራጭ አድርገን ስንወስድ ብቻ ነው፡፡

በአጠቃላይ የደን ልማቱ ስራ ለራስ ፣ ለትውልድና ለሃገር የሚሰራ ስራ መሆኑን ተገንዝበን ለአላማው መሳካት በጋራ መቆም ተገቢ ነው፡፡ እንደመንግስትም ስለአረንጓዴ አሻራ ደጋግሞ በሚዲያ ማስነገር ብቻውን ለውጥ አያመጣም፡፡ ይልቁንም ዘርፉ ከፍተኛ በጀት እንደሚፈልግ ተረድቶ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል በጀት መድቦ በጥንቃቄ እንዲመራ የሚያስችሉ ስራዎችን ከወዲሁ መስራት ያስፈልጋል፡፡ በእኛ በኩል ይህን እንደሀገር የተጀመረውን የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብር በተባበረ ክንዳችን ለትውልድ አፅንተን እናውርስ ፤ ዛሬ ላይ የተጣለብንን ኃላፊነት ሁላችንም በአግባቡ እንወጣ እንላለን ሠላም፡፡

# ምርጥ ምርጡን

በፍሬው ምናለ

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ ከሸዋው ንጉሥ ኃይለ መለኮት ሣህለ ሥላሴ እና ከወ/ሮ እጅጋየሁ ለማ ነሀሴ 12 ቀን 1836 ዓ.ም በአማራ ምድር በሸዋ ክፍለ ሀገር አንኮበር ተወለዱ። የአፄ ልብነ ድንግል ልጅ ከሆኑት ከአፄ ያዕቆብ ትውልድ 13ኛ የዘር ሐረግ ይቀመጣሉ። ልጅ ምኒልክ በ11 ዓመታቸው አፄ ቴወድሮስ ወደ ሸዋ በመጡ ጊዜ ይዘዋቸው ወደ ጎንደር ሄደው ነበር። በ1857 ዓ.ም ከወሎና ከሸዋ ባላባቶች ጋር ውስጥ ውስጡን ሲላላኩ ቆይተው ከመቅደላ አምልጠው ወደ ሸዋ ገቡ። 10 ዓመትም በግዞት ነበሩ።

ከግዞት ዘመን በኋላ ወደ ሸዋ ደብረ ብርሃን ተመልሰው በአባታቸው ዙፋን ተቀምጠው ንጉሥ ምኒልክ እየተባሉ ለ12 ዓመታት ያህል እስከ 1870 ዓ.ም ተቀናቃኝ ሳይኖርባቸው ሸዋን ሲገዙ ቆዩ።ንጉሥ ምኒልክ ኃይላቸውን እያጠናከሩ ሲመጡ አፄ ዮሐንስ ስጋት ገባቸውና ሸዋን ለማስገበር ወደ ደብረ ብርሃን መጡ። የፈሩት ሳይደርስ ቀረና ንጉሥ ምኒሊክ ለአፄ ዮሐንስ እገብራለሁ የሚል መልዕክታቸውን ከላኩ በኋላ ደብረ ሊባኖስ ሄዱና በአካል ተገኝተው ሲስማሙ አፄ ምኒልክ ንጉሥነታቸው ሙሉ እውቅና ሊያገኝ ችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ንጉሥ ምኒልክ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ሰዎችን ወደ ሸዋ አምጥተው በክብር እያሳደጉ፣ እያስተማሩ፣ ግዛትና ሹመት እየሰጡ፣ በጋብቻና በባህል እንዲተሳሰር፣ አንዱ የአንዱን ጎሳና ሃይማኖት እንዲያከብርና ተስማምቶ እንዲኖር አድርገዋል። ሰው ባሪያ አይባልም በማለት ከልክለው አስተምረዋል።

ንጉሥ ምኒልክ ጥቅምት 25 ቀን 1882 ዓ.ም በጳጳሱ በአቡነ ማቴወስ እጅ ተቀብተው ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ተብለው እንጦጦ ማርያም ቤተክርስቲያን ነገሡ። በሦስተኛውም ቀን ወ/ሮ ጣይቱ ብጡል በጳጳሱ በአቡነ ማቴወስ እጅ የሚገባቸውን ዘውድ ደፍተው እቴጌ ተባሉ። ከዚያ ቀን ጀምሮም "ጣይቱ ብርሃን ዘኢትዮጵያ" እየተባሉ መጠራት ጀመሩ። ዳግማዊ ምኒልክ የተባሉትም የንግሥተ ሳባና የሰሎሞን ልጅ ምኒልክ ቀድሞ ነግሦ ስለነበር ነው።

ዳግማዊ አፄ ምኒልክ በህይወት ዘመናቸው ካከናወኗቸው በርካታ አኩሪ ታሪኮች መካከል ደራሲ አቤ ጉበኛውና ሕይወቱ በሚለው መጽሐፋቸው በእርሳቸው የንግሥና ዘመን የተመሠረቱ ተቋማትን እንዲህ ይዘረዝሯቸዋል። ፦ ስልክ በ1882፣ ፖስታ፣ የውሃ ቧንቧ እና ገንዘብ በ1886 ፤ የፅህፈት መኪና በ1887 ፤ ኤሌክትሪክ፣ ዘመናዊ ህክምና እና ቀይ መስቀል በ1889 ፤ ሆስፒታል በ1890 ፤ ወፍጮ በ1891 ፤ ባቡር በ1893 ፤ ባንክ ፣ ማተሚያ እና ሆቴል በ1898 ፤ አውቶሞቢል ፣ ጋዜጣ እና የሚኒስትሮች ሹመት በ1900 ፤ ፖሊስ በ1901 እና ፋርማሲ በ1904 ዓ.ም እንደተቋቋሙ ታሪካቸው ያስረዳል። ባጭሩም ቢሆን የዳግማዊ አፄ ምኒልክን ታሪክ ያነሳነው ያለምክንያት አይደለም። የአሁኑ ትውልድ ከእርሳቸው ታሪክ ምርጥ ተሞክሮ ወስዶ የሀገር ተቆርቋሪነትን፣ ጀግንነትን፣ አንድነትንና የአባቶችን ወኔ ተላብሶ ኢትዮጵያ ታሪኳን፣ ነጻነቷን፣ ክብሯንና ልዕልናዋን እንደያዘች ማስቀጠል እንዲችል ነው። ለዚህም ሐዲስ መጽሄት በባህልና ታሪክ አምዷ ምሁራንን አነጋግራ ቀጣዩን ሀሳብ ይዛ ቀርባለች። ተከታተሉ መልካም ንባብ።

የዚህ አምድ እንግዳ ታደሰ አክሎግ (ዶ/ር) ናቸው። ታደሰ አክሎግ በባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሣይንስና ዓለም አቀፍ ጥናት የትምህርት ክፍል መምህር፣ ተመራማሪና ረዳት ፕሮፌሰር ሲሆኑ በቀረቡት ጥያቄዎች መሠረት ተከታዩን ማብራሪያ ሰጥተውናል።

አፄ ምኒልክ በርካታ አወንታዊ ተግባራት አሏቸው፤ ለሀገራችን ብቻ ሳይሆን ለአፍሪካና ለዓለም ሊተርፉ የሚችሉ አርአያነት ያላቸው ንጉሥ ነበሩ ። አርቆ አሳቢነታቸው የተመሰከረላቸው፣ ታላቅ ሀገር ለመመስረት ራዕይ ሰንቀው የተሠማሩበት ሁሉ የተሳካላቸው፣ በቅኝ ግዛት ዘመን ከብዙ ኃይሎች ጋር ተጋፍጠው የሀገሪቱን አንድነትና ነጻነት ላለማስደፈር ህልውናዋን በመጠበቅ፣ በማስከበርና በመከላከል ረገድ ከውጭ ወራሪ ጠላት ጋር ያደረጉት እንቅስቃሴ ጉልህ ሚና የነበረው ሲሆን ለአሁኗ ኢትዮጵያም መሠረት የጣሉ ባለ ራዕይና ታዋቂ ንጉሥ ነበሩ።

ዘመናዊነት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ሀሳብ አመንጭተው ተግባራዊ አድርገዋል። የህዝቡን አዲስ ነገር (ባህል ) የመቀበል አስቸጋሪ ባህሪ ተቋቁመው ራሳቸው ፋና ወጊ በመሆን ሠርቶ አሰሪ የትህትና መሪ ነበሩ። ምንም ዓይነት ማዕርግ ይኑራቸው ከውጭ ሀገር ከሚመጡ መሪዎች ጋር በመግባባት



ዳግማዊ አፄ ምኒልክ

ንጉሡ ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ለማወቅ የፈለጉትን ቴክኖሎጂ እየጠየቁ በመማር ራሳቸውን የሚያበቁ፣ በመረጃና በእውቀት የሚያምኑ ብልህ ንጉሥ ነበሩ፡፡ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነታቸው ጠንካራ ስለነበር ቴክኖሎጂ ባላደገበት በአድዋ ጦርነት ወቅት በዓለም አቀፍ ደረጃ የመረጃ ፍሰት እያገኙ አውሮፓውያን ምን እየሰሩ እንዳለ ማንኛውንም ወቅታዊ መረጃ ከውጭ በሚጻፉ ሰነዶች የሚያገኙበት ስርዓት ነበራቸው፡፡

በሰብአዊ መብት ረገድም የሀገራቸው ህዝብ መብቱ የተከበረ እንዲሆን ጥረት ያደርጉ ነበር፡፡ ለምሳሌ ነገሥታትን ይፈትን የነበረው የባርነት ስርዓት እንዲቆምና የሴት ልጅ እኩልነት እንዲረጋገጥም በርካታ ስራ ሰርተዋል፡፡ ለምሳሌ ሆቴል አቋቁመው ባለቤታቸው እቴጌ ጣይቱን እንደ ሞዴል በመጠቀም እቴጌይቱ የሆቴሉ አስተናጋጅ ሆነው እንዲሰሩና የእደ-ጥበብ ስራ ለወይዛዝርቱ እንዲያስተምሩ በማድረግ የለውጥ መሪ ነበሩ፡፡

አውሮፓውያን ስልጣኔ ከእኛ ወዲያ ላሳር ነው፤ ኢትዮጵያን ልናሰለጥን ነው የመጣን፤ በማለት ሲኩራሩ ንጉሡ በእንዲህ ዓይነት ሥራቸው ማን የሰለጠነ እንደሆነ በማሳየት አሳፍረዋቸዋል፡፡ የአውሮፓውያን የቅኝ ገዢዎችን አሰላለፍና የእድሜያቸውን መግፋት በማስተዋል የሚኒስትሮች ምክር ቤት አቋቁመውና መንግሥታቸውን ተቋማዊ አድርገው ማለፋቸውም ተተኪ ማፍራታቸውን ያሳያል፡፡

ሕዝቡ በንጉሡ አዋጅ ለአድዋ ጦርነት ሲጠራ የነበረውን የመዝመት ፈቃደኝነትና የጋለ ስሜት ወደ አሁኑ ትውልድ ለማስተላለፍ መጀመሪያ የሚታይና የሚተገበር ቅድመ-ዝግጅት አለ፡፡ አሁን ኢትዮጵያ ላይ መሪውም ሆነ ተመሪው ብዙ ነገር አጥቷል፤መመሪያና አቅጣጫ በማውረድ ብቻ ተግባሩ መሬት አይነካም ፡፡ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ህዝብ ለለውጥና ለልማት የሚያነሳሳው ስለሚፈልግ አሁን የዴሞክራሲ ስርአት ጅምር አለ በሚባልበት ወቅት ያልተሰራውን አፄ ምኒልክ እያንዳንዱን ተግባር ወደ ታች ወርደው ቅድሚያ እየሰሩ በማሳየታቸው ህዝቡን እንዲከተላቸው ማድረግ ችለዋል፡፡

ሁሉም ሕዝብ ጥሪውን ተከትሎ ለአድዋ ጦርነት ሆ! ብሎ የወጣበት የመጀመሪያው ምክንያት በታሪክ የኢትዮጵያ ህዝብ ከውጭ ለሚሰነዘር ወራሪ ኃይል አፃፋውን ለመመለስ የታወቀ ሲሆን ዳግማዊ አፄ ምኒልክን ያክል ትክክለኛ መሪ ማግኘቱ በተጋጋለና ዕፁብ ድንቅ በሆነ ባለቤትነት ወደ ዘመቻው እንዲያመራ አድርጎታል፡፡ ጥሪውን ያስተላለፉበት መልእክት፣ የተጠቀሙት ሀሳብና ቃላት መሳጭ እና ሳቢ ነበር፡፡ ለምሳሌ ጠላት ሃይማኖትህን፣ ትዳርህን፣ ባህልህን፣ ብሎም ሀገርህን ሊያሳጣህ ዘምቶብሃልና አሁኑኑ ተገቢውን ምላሽ ስጥ የሚል ነበር፡፡ ህዝቡም የሀገሩን ህልውና ለማጥፋት የመጣ ጠላት መሆኑን በመገንዘብ እያንዳንዱ ጉልበት ያለው በጉልበቱ ደካማው በጸሎቱ የሚችለውን ጠጠር እንዲወረውር አስችሎታል፡፡ የዘመቻ ጥሪው ወራሪው አስከፊና በህዝቡ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት የሚያሳይ ብቻ ሳይሆን የንጉሡ ታማኝነት ትልቅ ቦታ ይዞ ስለነበር ነው፡፡ ስለዚህ

# ባህል/ታሪክ



"አግላይነትንና ተፈናቃይነትን እንደ ባህል ያደረገ ትውልድ ይዘን ኢትዮጵያን ልንገነባት አንችልም፡፡"

ታደሰ አክሎግ (ዶ/ር)

የአሁኑ ትውልድ (ከላይ እስከ ታች ያለው አመራርና ፈጻሚ) ታማኝነትና ሕዝባዊነት ባህሪ ሊኖረው ይገባል፡፡

ንጉሡ ህዝቡን በነቂስ በዘመቻ እንዲወጣ ያደረጉበት ስልት ለአሁኑ ትውልድ ተላልፎ ጠቃሚ እንዲሆን ማየት ያለብን እኛ የኢትዮጵያ ብሎም የምስራቅ ስልጣኔ የምንለው በፈጣሪ ኃይል የሚመካ ህዝብ ያለን ነን እንጅ እንደ ምዕራባዊያን በጡንቻ የምናምንና የዳርዊንን አስተሳሰብ የምናራምድ አለመሆናችንን ነዉ፡፡ ፕሮፖጋንዳ ሀሰትን እውነት ለማስመሰል ደጋግሞ በመናገር ላይ የተመሰረተ የፖለቲካና አመራር ጉዳይ ብዙ ጊዜ ኢትዮጵያ ውስጥ ተፈትኖ ወድቋል፡፡ ህዝብንና መንግሥትን ሆድና ጀርባ ያደረጋቸው ይህ እንደሆነም ሊታወቅ ይገባል፡፡

ያሰብነውና ያለምነው ፍትሕ፣ ሰላምና አንድነት የሚመጣው መንግሥትና ህዝብ ተናበው እየሠሩ መኖር ሲችሉ ብቻ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ መሪው የሚከተሉትን ባህርያት መላበስ ይኖርበታል፡፡ ሀቀኝነትን፣ ታማኝነትን፣ ግልጸኝነትን፣ ትህትናን፣ የሀገርንና የህዝብን ጥቅም ማስቀደምንና የመሳሰሉትን የራሱ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ የህዝብን ስነ ልቦና ፈትሾና የልብ ትርታውን አዳምጦ ችግሩን ለመፍታት ጥረት ሲያደርግ ህዝቡ ሆ! ብሎ አመራሩን መከተል ብቻ ሳይሆን አድርግ የተባለውን ሁሉ በባለቤትነት ያከናውናል፡፡ ምክንያቱም የአጼውን ሰርቶ የማሰራት ሞዴል መከተል የአማራጮች ሁሉ ቁንጮ ነውና፡፡

ኢትዮጵያ ጣልያንን የማሸነፏ ምስጢር ለአውሮፓዊያን እንቆቅልሽ ሆኖባቸው ቆይቷል፡፡ ምክንያቱም ነጮች ነጭ የበላይ ጥቁር የበታች ብለው ስለሚያምኑ ይህ ድል የዓለም ሀገራትን ያነጋገረ ትልቅ አጀንዳ ሁኖ አልፏል፡፡ ይህ ድል ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትኩረት ውስጥ ገብታ እንድትጠና የተደረገችበትን ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ ምን አልባትም የአውሮፓዊያን ተጽዕኖ በጉልህ እንዲታይ የሆነው በአድዋ ድልና በአጼ ምኒልክ አመራር ሁኔታ ነው ተብሎ ይነገራል፡፡

የአድዋ ጦርነት ለኢትዮጵያዊያን ፍትሀዊ መሆኑ ብቻ ሣይሆን መሪ እና ተመሪ እጅና ጓንት መሆናቸው ለድሉ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ነበረው፡፡ የህዝቡንና የመንግሥትን ጠንካራ አንድነት የፈጠረው ደግሞ የንጉሡ የአመራር ጥበብ እንደነበር አያጠራጥርም፡፡ በዋናነት የድል ባለቤት መሆን የተቻለው ደግሞ አጼ ምኒልክ ከነባለቤታቸው ዘምተው ጦሩን በመምራታቸውና ሁሉም ኢትዮጵያዊ አምኖበት በቁርጠኝነት ስለተዋጋ መሆኑን ታሪክ ያስረዳናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ኢትዮጵያዊያን በፈጣሪ የሚያምኑ ሕዝቦች በመሆናቸው በዚህ ድል የፈጣሪ እገዛም እንዳለበት አምናለሁ፡፡

በአንጻሩ ይህ ጦርነት ለወራሪው ፍትሀዊ ባለመሆኑና እንደ ኢትዮጵያ በቆራጥነት መታገል ባለመቻሉ ድሉ ለኢትዮጵያ ሊሆን ችሏል፡፡ እንደሚታወቀው የአድዋ ድል ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ለሞት እሽቅድምድም በሚመስል መልኩ ተረባርበው በደምና በአጥንት ያመጡት ስለመሆኑ ዓለም ያወቀውና ዘመን የማይሽረው አስደናቂ ሀቅ

ነው፡፡ ይህ ድል በዓለም ላይ ምዕራባዊያን ኃይል ምንድን ነው? ብለው ሲለኩ የወታደርና የዘመናዊ መሣሪያ ብዛት አለመሆኑን ያረጋገጡበትና ያንን የሚመኩበትን የኃይል ትርክት ያስቀየረና ኃይል ሞራልና የስነ - ልቦና ቁርጠኝነት እንደሆነ ለዓለም ያስተማረ ትልቅ ትምህርት ቤት ሆኖ አልፏል፡፡

የአሁኑ ትውልድ ከዚህ ዓለም አቀፋዊ ድል ለመማር መጀመያ ራሱንና የአሁኗ ኢትዮጵያ በርካታ ችግሮች ያሉባት መሆኗን ማየት ይገባዋል፡፡ ይህ ችግር በጊዜ ካልተፈታ ፈተናው ከሀገር መቀጠልና አለመቀጠል ብቻ ሣይሆን በሀገሪቱ ውስጥ የዘላቂ ሰላም እጦት፣ የኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ ችግር መስፋፋትና የባህል መሸርሸርም ሌላኛው ተግዳሮት ነው፡፡

ሀገራዊ አንድነትን የሚሸረሽረው ዋናው ችግር የአሁኑ ትውልድ ብሔር የሚለውን ቃል የሚጠቀምበት አግባብ የተሳሳተ ስለሆነ ነው፡፡ በፖለቲካል ሣይንስ ብሔር ማለት ሀገር እንጅ ነገድ ማለት አይደለም፡፡ ትክክለኛ ትርጉሙ ይህ ስለሆነ የኢትዮጵያ እያንዳንዱ ብሔር የራሱን ሀገር ለመመሥረትና ለማሳደግ ጥረት ያደርጋል እንጅ ወደ አንዲቷ ኢትዮጵያ ለመምጣት አይፈልግም፡፡ ሕወሀት ታላቋን ትግራይ እንመሠርታለን ለማለት የበቃውም በዚህ ተጨባጭ ምክንያት ነው፡፡ ይህ አካሄድ የራሽያ ፖለቲከኛ ጆሴፍ እስታሊን ብሔርን እንደ ነገድ ቆጥሮ ሶቭየት ኅብረትን የበታተነበት ዘዴ ስለሆነ ለኢትዮጵያ አይጠቅማትም፡፡ ሕብረ- ብሔር ሲባልም የሀገሮች ጥምረት (united nation) እንደ ማለት ነው፡፡

መያዝ ያለበት ኢትዮጵያ የብዝኀ - ነገድ፣ እምነት፣ ባህልና ቋንቋ ሀገር ስለሆነች የተለያዩ ባህሎችና ቋንቋዎች ማደግ አለባቸው ያስማማል፡፡ ሀገራዊ አንድነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ ነገድ የራሱን ቋንቋ፣ ባህል፣ እምነት ወዘተ በማስፋፋትና በማሣደግ መጠቀም ተገቢና ፍትሐዊ ነው፡፡

ትውልዱ ከዚህ ችግር ለመውጣት ቅድሚያ ለሚሰጠው ቅድሚያ እየሰጡ የላላውን አንድነት ቀስ በቀስ እያጠበቁ አስፈላጊውን ሥራ መሥራት ተገቢ ይሆናል፡፡ ሕዝባዊ አንድነትን አጠንክሮ፣ የመንግሥትንና የሀገርን ጥምረት አዳብሮና ሰላምን አስፍኖ ለመምራት ከአጼ ምኒልክ መማር ይገባል፡፡

አፄ ምኒልክ ከሁሉም ነገሥታት በተለየ ሁኔታ እምየ የተባሉበት ምክንያት ምን እንደሆነ ማየት ተገቢ ይሆናል፡፡ እምየ ለእናት የሚሰጥ ስም ነው፤ እናት ደግሞ የደግነት፣ የርህሩህነትና የተንከባካቢነት ባህሪ ያላት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ንጉሡም ይህን ባህሪ የተላበሱ ስለሆኑ ነው፡፡ ማሣያዎቹን ስንመለከት በኢትዮጵያ ክፉ ቀን በሚባልበት ከ1882 እስከ 1884 አካባቢ የተራቡ ወገኖች ወደ ቤተ መንግሥት ይጐርፉ ነበር፡፡ በረሀቡ ምክንያት እርሳቸው በሀዘንና በጸሎት ከመወሰናቸውም በተጨማሪ ባለቤታቸው ጋር ሕዝቡን ይመግቡ ነበር፡፡ ሁሉም ተሰብስቦ አንድ እንጀራ እየተቆረሰ ለሁለት ለሦስት የሚበላበት ሁኔታ ስለነበር ዛሬ ቡፌ የሚባለው ያን ጊዜ የተጀመረ ነው ይባላል፡፡ ይህን የደግነት አገልግሎት ከእርሣቸው በኋላ የመጡት ተግባራዊ አላደረጉትም፡፡ ለምሣሌ አፄ ኃይለ - ሥላሴ የወሎ ሕዝብ ተርቦ ሣለ አይደለም መመገብ የተራበው ዜጋ ወደ አዲስ አበባ እንዲመጣ አልፈለጉም ነበር፡፡

ንጉሡ ግብር ሲያበሉም በአንድ ጊዜ ወደ አራት ሺህ ሰው ይመገብ ነበር፤ በዚህ መጠን በቀን ሶስት አራት ዙር የሚጋበዘዉን የተመለከተና በፕሮግራሙ የታደመ አንድ ፈረንጅ "የአዲስ አበባ ሕዝብ 50 ሺህ ቢሆን አንድ አምስተኛው ሕዝብ ተጋባዥ ሆነ ማለት ነው፡፡" ሲል በመደነቅ ተናግሯል፡፡ ሌላኛው ምክንያት በሀገር ጉዳይ በተደረጉ ጦርነቶች አፄ ምኒልክ ሰላምን ያስቀድማሉ፤ እብሪተኛ ከሆነ ይዋጋሉ፤ወታደሩ ሲማረክ ወይም ሲቆስል እግሩን አጥበው፣ አሣክመውና አድነው ስልጣን ይሰጡ ነበር፡፡ ሌላው ቀርቶ በአድዋ ጦርነት የተማረኩትን ወራሪ የጣሊያን ወታደሮች እርሣቸው እንኳን ሊገድሏቸው አስፈላጊውን እንክብካቤ አድርገው በሰላም ወደ ሀገራቸው መልሰዋቸዋል፡፡ የእርሳቸው የእናትነት ስያሜ የመጣው ሠርተው ባሣዩት ውጤት እንጅ እንደ እንግዳ ደራሽ አለመሆኑን ልብ ይላል፡፡

የአሁኑ ትውልድ ከስያሜያቸውና ከተግባራቸው ለመማር ከኢትዮጵያ አንፃር መሪዎች አርአያነት ያለው የሞራልና የሥነ ምግባር ተግባራትን የመፈፀም ኃላፊነት ይጠበቅባቸዋል፡፡ እንደ ውጩ አባባል መሪ የተገኘ ከሕዝብ በመሆኑ መሪው ሕዝብን ይመስላል ይባላል፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ግን ሕዝብ መሪውን ይመስላል የሚለው በአፄ ሚኒልክ እውን ሆኗል፡፡ ከባህላችን፣ ከእምነታችንና ከስልጣኔያችን ውጭ የሚደረጉ የምዕራባውያን ባህልና አላስፈላጊ ስልጣኔ ለሕዝብም ሆነ ለሀገር ስለማይጠቅም ትርክቱን ማስተካከል ይገባል ፡፡

ዝቅ ብሎ ለሕዝብ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት እንጂ ከሞራል ህጐች የወጣ በኃይልና በገንዘብ በማመን አንዴ በሕዝብ ምርጫ ስልጣን ይዣለሁ በሚል አላስፈላጊ እንቅስቃሴ ማድረግ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ በተለያየ አመለካከት የስልጣን ትግል ሊኖር ይችላል እንጅ ሕዝብን ታርጌት ያደረጉ ጥቃቶችን፣ ጭፍጨፋዎችንና መፈናቀሎችን ሀገራችን በታሪክ አስተናግዳ አታውቅም፡፡ ስለዚህ የሚሻለው እነዚህን ተግዳሮቶች አስወግዶ በምትኩ ከአፄው ስያሜና ተግባር መልካም ተሞክሮ ለመውሰድ ሕዝብን

# ባህል/ታሪክ

ማዕከል ያደረጉ መልካም ግንኙነቶች፣ ዘላቂ ሰላምና ፍቅር፣ መተሳሰብና መረዳዳት፣ የሕዝብ ተጠቃሚነትና አንድነት ወዘተ ተስፋፍተው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡

ከቀደምት አባቶቻችን ተምረን ከገባንበት ቀውስ ለመውጣት ፖለቲከኞች ትልቁን ሥዕል መርከቧን ይመልከቱ ነው የምለው፡፡ ኢትዮጵያ የምትባል መርከብ የመስመጥ እድሏ እየተቃረበ ነው፡፡ የሚተርፈው ማን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ ይችን መርከብ እንድትሰጥም እያደረጋት ያለው ማንና ምንድን ነው? ብሎ ነቅሶ ማውጣት ያስፈልጋል፡፡ ኢትዮጵያን የምናይበት እይታ ትርክቱ የተዛባ መሆኑን ማስተዋል ይገባል፡፡ የነበረችውን ታላቋን ኢትዮጵያ እንዳልነበረች የማድረግና ልንኮራበት የምንችለውን የአድዋን ድል ሣይቀር እንድናፍርበት ተደርጐ የሚነገርበት እና ትውልዱ በዚህ መልኩ የተቃኘበት ስለሆነ ቢገዳደል አይፈረድበትም፡፡ ምክንያቱም የነበረን እውነተኛ ታሪክ ተገልብጦ የነገድ ጦርነት ስታካሂድ የቆየች ሀገር ናት ተብሎ ነው የቀረበው፡፡ አንዱ ነገድ ጨፍጫፊ ሌላኛው ተጨፍጫፊ በሚመስል ነገር ለትውልዱ የተሣሣተ ትምህርት በሚዲያ፣ ሥርዓተ - ትምህርት ተቀርፆ፣ በመጻሕፍት ተዘጋጅቶና ታትሞ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒበርሲቲ ድረስ ተስፋፍቶ የተሰጠ ስለሆነ በቀላሉ የሚጠፋ አይደለም፡፡ ይህ ከእንቅልፍ የመንቃት፣ የመዘጋጀትና የመሮጥ ትግልን ይጠይቃል፡፡ ትልቅ የአስተሣሰብ ለውጥ ማምጣት ቁልፉ ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ይህን ከተረዳን ሌሎችን የኢኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮች ቀስ በቀስ መፍታት ይቻላል፡፡ በአንጻሬ እንደ አደጉና መካከለኛ ሀገሮች መሆን አይቻልም፡፡ የሕዝባችንን ሰላምና አንድነት ካረጋገጥንና ሁሉም በየሥራ ዘርፉ ተሠማርቶ የሚሠራበትን ነባራዊ ሁኔታ ከፈጠርን መሪና ሕዝብ እጅ ለእጅ ሆኖ ልማትን፣ ዴሞክራሲያዊና ፖለቲካዊ መረጋጋትን ማስመዝገብ ይቻላል፡፡ ትልቁ ነገር መርከቡ ከሰመጠ ነው፡፡ ሀገራችንን ከሚያጠፋ የተሣሣተ እና የጨቋኝ ተጨቋኝ አስተሣሰብ ትርክት ያልወጣ እና አግላይነትንና ተፈናቃይነትን እንደ ባህል ያደረገ ትውልድ ይዘን ኢትዩጵያን ልንገነባት አንችልም፡፡

የምኒልክ ኢትዮጵያ ማለት ለአፍሪካዊነት መነሻ ነበረች፤ አፄ ምኒልክ ከእንግሊዝና ከፈረንሣይ ጋር የሚያደርጉት የዲፕሎማሲ ሥራ የአፍሪካን መሪዎች በማነሳሳት እነዚህን ነጭ ወራሪዎች በጋራ እንመክት ይሉ ነበር፡፡ አፄ ሚኒልክ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ አውሮፖና አሜሪካ የነበሩ ጥቁሮች ድጋፍ ያደርጉ ነበር፡፡ በኋላ አፄ ኃይለ ሥላሴ ፖን አፍሪካኒዝም እውን ያደረጉት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (pan africanism) አፍሪካዊነት ስሜት አስተሣሰብና እንቅስቃሴ በአፄ ምኒልክ ተጀምሮ ነበር፡፡

ቀደም ሲል በኢትዮጵያ መሪነት የነበረው ከፍተኛ አፍሪካዊ እንቅስቃሴ የኮሰመነው ኢትዮጵያ ስለኮሰመነች ነው፡፡ የኢትዮጵያ አንድነት ወደ ቀድሞ ቦታው ከተመለሰ አሁንም ኢትዮጵያ የአፍሪካ መሪነትን ትይዛለች፡፡

በመጨረሻ መልእክታቸው የአድዋ አንፀባራቂ ድል የመጣው በዋናነት ከውጭ ወራሪ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ የአሁኑ ትውልድ የገጠመው ፈተና እንደምናየው የውስጥ ችግር ስለሆነ መፍትሔውም ለየት ያለ ሊሆን ይገባዋል፡፡ በመሪዎች በኩል ሆደ - ሰፊነት አርቆ አሣቢነት፣ ግልጸኝነት፣ ተጠያቂነትና የህዝብን ችግር የሚረዱ መሆን ይጠበቃል፡፡ በዘመነ ሉላዊነት የሰፈር ቋንቋና ነገድ ተኮር ፖለቲካ የትም አያደርስም፤ የሚጠቅምም አይደለም፡፡ ስለሆነም በህዝቡ መካከል አንድነት፣ የኢኮኖሚ እድገት፣ ፍትሐዊ ሀብት ክፍፍልና የሙብት ጥበቃ እንዲኖር መሥራት ያስፈልጋል፡፡ በአሁኑ ሰዓት ያለው የእርስ በርስ ግጭት ብቻ ሳይሆን የሀገሪቱ ግዛትም ተደፋሯል ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ አመራሩ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስድ ሆኖ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለሀገር ደህንነትና አንድነት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያበረክት ይገባል፤ በማለት ሀሳባቸውን አጠቃለዋል፡፡

የዝግጅት ክፍሉም ከአፄ ምኒልክ የተገኙትን መልካም ተሞክሮዎች የአሁኑ ትውልድ በቅንነት ተቀብሎ ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት ያምናል፡፡ምክንያቱም "የአባቱን ቢሰጡት ሕይወቱ ቢነሱት ሞቱ" ይላልና፡፡ ይህ ሲባል ሕይወታቸውን በመገበር ደማቸውን አፍስሰው አጥንታቸውን ከስክሰው ኢትዮጵያን ከነሙሉ ነፃነቷ ለትውልዱ ያስረከቡትን አባቶች እንጅ በሕዝብና በሀገር ላይ የታሪክ ተወቃሽ ሆኖ ያለፈን ባንዳ ማለታችን እንዳልሆነ ሊታወቅ ይገባል፡፡

ከአፄ ምኒልክ ከተገኙ በረከቶች የተወሰኑት፡- አርቆ አሳቢነታቸው፣ ሕዝባዊነታቸው፣ የአመራር ጥበባቸው፣ ርህሩህነታቸው፣ የስልጣኔ በር ከፋች እና ፈጻሚና አስፈጻሚ መሆናቸው ሊጠቀሱ ከሚችሉ ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ስለዚህ የአሁኑ ትውልድ የንጉሡንና የሕዝቡን አንድነትና ፍቅር ወስዶ ሥራ ላይ እንዲያውለው በመጠቆምና ለሁሉም ሰላም ይቅደም በማለት የዘሬውን እዚህ ላይ አጠናቋል፡፡ ሰላም!



# የዘርፉ እምርታዎችና ተግዳሮቶች

በደፋሩ እምሬ

ትምህርት ለቴክኖሎጂ መሻሻል ፣ለማህበራዊ ለውጥና ለኢኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ መሣሪያ መሆኑ ይነገራል፡፡ከዚህ አኳያ በብዙ መልኩ የእድገት ማማ ላይ የተፈናጠጡ አገሮች ትምህርትንና የሰው ሀብታቸውን ከአገራቸው ልማት እንዲሁም አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ጋር አስተሳስረው መተግበር በመቻላቸው ነው፡፡ የዚህ ሚስጢር ደግሞ በፖሊሲ አቅጣጫ የተቀመጠ የሰው ሀይል ልማት በመከተልና ፖሊሲውንም ለመተግበር የሚያስችሉ የረጅምና የአጭር ጊዜ የትምህርት እቅዶችን በትጋት መፈጸማቸው እንደሆነ ይታመናል፡፡



“ትምህርት በአንድ ወገን ብቻ ውጤታማ ስለማይሆን የባለድርሻ አካላትን እገዛ ይፈልጋል”

አቶ ጌታቸው ቢያዝን

ኢትዮጵያም በትምህርት መሳሪያነት ሌሎች የበለፀጉ አገራት ከደረሱበት ለመድረስ ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረ ጀምሮ ለተቆጠሩት 120 አመታት የተለያዩ የማስፈጸሚያ ስልቶችን የርብርብ ማዕከል አድርጋ በእውቀት የዳበረ ዜጋን በጥራት፣በብዛትና በአይነት በማልማት ስትሰራ ዛሬ ላይ ደርሷለች፡፡ በተጨባጭም እንደሚታየው ከትምህርት የሚጠበቀው ውጤት ጥሩ እምርታ ላይ ይገኛል። በተማረ ሰው ሀይል ልማት፣ በትምህርት መሰረተ ልማት፣ በማህበረሰብ አስተሳሰብ ለውጥ ልማት፣ወዘተርፈ. እንደ አገር የተመዘቡት ሁሉ እድገት ላይ መሆኗን ማሳያዎች ናቸው።

በአማራ ክልልም እየተመዘገበ ዛሬ ላይ የደረሰው የዘርፉ ውጤታማነት ኢትዮጵያ በምትከተለው የትምህርት ፖሊሲ አቅጣጫ ስር የሚመራ ነው። ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሉ ከራሱ የህዝብ ብዛት እና አሰፋፈር፣ የቆዳ ስፋት፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበዊና ሌሎቸ ከትምህርት ዘርፉ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሚያያዙ ጉዳዮች አንጻር እየቃኘ የተመዘገበው እምርታ በመልካም ሁኔታ ቀጥሏል። ይህን እውነታ አስመልክቶም በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ትምህርት ቢሮ ህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት አቶ ጌታቸው ቢያዝን እንደገለፁት ዛሬ ላይ በክልሉ በአጸደ ህጻናት ደረጃ 627 ትምህርት ቤቶች፣ በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ 9559 እና በሁለተኛ ደረጃ 688 ትምህርት ቤቶች አገልገሎት ይሰጣሉ።

የከፍተኛ ትምህርት መሰረተ ልማትን በሚመለከት ደግሞ 10 ኮሌጆች በክልሉ ይገኛሉ። ዩኒቨርሲቲዎች ምንም እንኳን በፌደራል መንግስት የለሙና የሚተዳደሩ ቢሆንም በክልሉ ውስጥ 10 ዩኒቨርስቲዎች አሉ። ይህ በትምህርት መሰረተ ልማት ዙሪያ በክልሉ የተመዘገበውን እድገት የሚያሳይ መሆኑን ገልፀዋል።

ከላይ በተጠቀሱት ትምህርት ቤቶች በመቶ ሺዎችና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ተማሪዎች ይማራሉ። በ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን በአጸደ ህጻናት ትምህርት ቤቶች የተመዘገቡት ከ114 ሺህ በላይ ናቸው።

በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ከሁለት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች ተመዝግበዋል። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የተመዘገቡት ደግሞ ከ534 ሺህ በላይ ይሆናሉ።

ከመምህራን ብዛት ጋር በተያያዘ የ2016 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ከሁለት ሺህ 500 በላይ የአፀደ ህፃናት መምህራን በማስተማር ስራው ላይ በንቃት ተሳትፈዋል።

በአንደኛ ደረጃ ደግሞ ከ126 ሺህ 500 በላይ መምህራን ሲያስተምሩ ነበር። በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችም ከ36 ሺህ 800 በላይ መምህራን የመማር ማስተማር ስራቸውን አከናውነዋል። በክልሉ ባሉ ኮሌጆችና ዩኒቨርሰቲዎች ያለው የሰው ሀይል ቁጥር እንዲሁ ከፍተኛ መሆኑ ይታወቃል። እነዚህ ሁሉ አሀዛዊ መረጃዎች የክልሉ ትምህርት ዘርፍ ከሰው ሀይል ልማት አንፃር የደረሰበትን የእምርታ ደረጃ የሚያሳዩ ናቸው። ወደፊት ብዙ መሰራት የሚገባቸው የዘርፉ የቤት ስራዎች ቢኖሩም እስካሁን የተመዘገቡት ውጤቶች ምስጢር የጠራ እቅድ ታቅዶ ፈጻሚ አካላት በደንብ እንዲያውቁት ከተደርገ በኋላ በተረጋጋና በሰከነ መንገድ ተመርቶ ወደ ተግባር ተለውጦ የተገኘ ነው። ለአብነት ያህል በሁሉም የክልሉ ትምህርት ቤት ደረጃዎች የተማሪዎች ብዛት ከላይ በተገለፀው መጠን ልክ እንዲጨምር የተሰራው የተማሪ ምዝገባ ሂደት እጅን በአፍ የሚያስጭን ነበር፡፡ በአንዳንድ አካባቢዎች በአንድ ጀንበር የተማሪ ምዝገባ እቅዳቸውን መቶ በመቶ ያሳኩ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም ወረዳዎች ነበሩ፡፡ የክልሉ አፈጻጸምም የተሻለ ነበር ብለዋል አቶ ጌታቸው።

መማር ማስተማሩን በመምራትና ተማሪዎችን ውጤታማ በማድረግ ረገድ የ6ኛና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ክልል አቀፍ ፈተናቸውን ያለምንም ችግር ወስደዋል፡፡ በተመሳሳይ የ12ኛ ክፍል ተማሪዎችን ለብሄራዊ ፈተናዎች በማዘጋጀትና ፈተናውን ያለምንም ችግር እንዲወስዱ በማድረግ ረገድ አበረታች ስራ ተሰርቷል፡፡ የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል የትምህርት ቤት ወላጅ ግንኙነትን በማጠናከር ረገድ የተሰራው ስራም አበረታች ሆኖ ተመዝግቧ፡፡ ጠቅለል ተደርጎ ሲታይ 2016 ዓ.ም የትምህርት ስራውን በመደገፍና በመከታተል በተሻለ ጥረት የተሻለ ስራ የተከናወነበት አመት ሆኖ ማለፉን ተናግረዋል።

የክልሉ ትምህርት ዘርፍ ከላይ በተጠቃቀሱት አመርቂ ስኬቶች ቢታጀብም እንከን የለሽ ነው ማለት ግን አይደለም። የጥራት፣ የተደራሽነት፣ የፍትሀዊነት፣ አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች ከደረጃ በታች ሆኖ መገኘት፣ ወዘተ. ጉድለቶች አሁን ድረስ በዘርፉ ላይ ይስተዋላሉ፡፡

“የባሰ አለ አገርህን…” እንዲሉ አበው ከእነዚህ ተግዳሮቶች በባሰ መልኩ የክልሉን ትምህርት የጎዳው ከቅርብ አመታት ወዲህ ክልሉን ያጋጠመው ሁለት አውዳሚ ጦርነት ነው። የመጀመሪያዉ በህወሀትና ብልፅግና መካከል ለሁለት አመት ያህል /ከ2013 እስከ 2014 ዓ.ም/ የተደረገው ጦርነት የክልሉን ትምህርት ዘርፍ ለከባድ ውድመት ዳርጎት አልፏል። በተለይ ምስራቃዊው የክልሉ አካባቢ ጦርነቱ በቀጥታ የተካሄደበት ስለነበር በትምህርት ዘርፉ ላይ ያደረሰው የከፋ ስብራት ዛሬ ድረስ በአግባቡ አልተጠገነም፤ አላገገመም። በዚህ ጦርነት ከአራት ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶች የመውደምና የዘረፍ አደጋ ስላጋጠማቸዉ ከሶስት ነጥብ አምስት ሚሊዮን በላይ ህፃናት ከትምህርት ገበታቸው ተስተጓጉለዋል ፡፡

“የወደቀ ዛፍ ምሳር ይበዛበታል” እንዲሉ አበው ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ ደግሞ በብልፅግናና በአማራ ህዝባዊ ሀይል ፋኖ መካካል ላለፈው አንድ አመት ሙሉ በክልሉ ሲካሄድ ቆይቶ ዛሬ ድረስ በቀጠለው ጦርነት ዘርፉ ለሌላ ሁለተኛ ዙር ስብራት ተዳርጓል። በዚህ ዙር ጦርነት በዘርፉ ላይ የደረሰውን የጉዳት ደረጃ በሚያሳየው ገለጻቸው “በበጀት አመቱ በክልሉ ካሉ በርካታ ትምህርት ቤቶች መካከል ከአራት ሺህ በላይ የሚሆኑት ተዘግተዋል፡፡ ከአንድ ሺህ አንድ መቶ በላይ ትምህርት ቤቶች በደረሰባቸው ጉዳት የውስጥ ቁሳቁሳቸው ወድሟል፡፡ ከሁለት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች ከትምህርት ገበታ ውጭ ሆነው ውድ ጊዜያቸውን ያለትምህርት እንደዋዛ አሳልፈዋል፡፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ሲያስተምሩ የነበሩ መምህራንና የትምህርት አመራሮች ከመደበኛ ስራቸው ተስተጓጉለዋል፡፡ በዚህም የተነሳ በክልል አቀፍና ብሄራዊ ፈተናዎች ላይ መቀመጥ የነበረባቸው ተማሪዎች ሳይፈተኑ ቀርተዋል፡፡ ይህም በተማሪዎች፣በመምህራና በተማሪ ወላጆች እንዲሁም በማህበረሰቡ ዘንድ ትልቅ የስነ ልቦና ጫና ፈጥሯል ብለዋል።

ከላይ የቀረበው መረጃ የሚያሳየው ትምህርትና ሰላም ምን ያህል ጥብቅ ትስስር እንዳላቸው ነው። ሰላም ከሌለ ትምህርት ቤት ይዘጋል፤ ይወድማል፤ ይፈራርሳል። ተማሪም ሆነ መምህር ስለማይኖር የሙያዎች ሁሉ መሰረት የሆነው የመማር ማስተማሩ ስራ ይቋረጣል።

የትምህርት ዘርፍ ከሚያቅፋቸው አያሌ ተቋማት፣ ከሚያሳትፈው ግዙፍ የሰው ሀይል አንጻር፣ወዘተ. አኳያ የሰላም መደፍረስ ሲከሰት የሚደርሰው ጉዳት መጠነ ሰፊና በቀላሉ የሚመለስ አይሆንም። በክልሉ ዛሬ ላይ በተጨባጭ የሚስተዋለው እውነታም ይኸው ነው።

“ህልም ተፈርቶ…” እንደሚባለው በክልሉ እየተካሄደ ያለው የሰላም መደፍረስ በትምህርት ስራው ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳደረ ቢሆንም ችግሩን ተቋቁሞ የዘርፉን መደበኛ ተግባራት በመፈፀም ረገድ ከቢሮ እስከ ወረዳ ድረስ ያለው መዋቅር እጁን አጣጥፎ ሳይቀመጥ በርካታ ስራዎችን ማከናወኑን የገለፁት አቶ ጌታቸው “ሚዲያዎችን በመጠቀምም ትምህርት ቤቶች የህብረተሰቡ በመሆናቸውና የሚያገለግሉትም ህበረተ



በሰሜኑ ጦርነት ወቅት የትምህርት ቁሳቁሶች ከወደመባቸው የምስራቅ አማራ ትምህርት ቤቶች መማሪያ ክፍሎች መካከል የአንዱ ክፊል እይታ

ሰቡንና ልጆቹን በመሆኑ ግጭቱ ትምህርት ላይ ተጽዕና እንዳያሳድር የሚያስገነዝቡ መግለጫዎች በተደጋጋሚ መሰጠታቸውን" ጠቁመዋል፡፡

ከትምህርት አመራሮች፣ ከባለሙያዎች፣ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ባለድርሻ አካላት ጋር ሰፊ ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ ክልላዊና ዞናዊ እንዲሁም በወረዳ ደረጃ የትምህርት ንቅናቄ መድረኮች ተካሂደዋል፡፡ በመድረኮችም ማህበረሰቡ የትምህርትን አላማና ግብ ተረድቶ ትምህርት ቤቶች እንዲከፈቱና ትምህርት እንዲጀመር አነሳስቷል፡፡ ቀደም ብለው የታተሙ መጻህፍት ስርጭትን በእቅድ በመምራት ወደ ወረዳዎችና ትምህርት ቤቶች ማድረስ አስችሏል።

ክልል አቀፍ የ6ኛ እና 8ኛ ክፍል ፈተናዎችን ከክልል እስከ ትምህርት ቤት ድረስ የፈተና ግብረ ሀይል ተቋቁሞ መፈተን የሚችሉ የ6ኛ እና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ፈተና ላይ እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡ የ6ኛ ክፍል ፈተናን ከወሰዱ ከ132 ሺህ 225 ተማሪዎች መካከል 97 ሺህ 859 ወይም 74 በመቶ ተማሪዎች 50 በመቶ እና በላይ ውጤት አምጥተዋል፡፡

ከ8ኛ ክፍል አንጻር ደግሞ ፈተናውን ከወሰዱት 149 ሺህ 950 ተማሪዎች መካከል 56 በመቶ የሚሆኑት 50 በመቶ እና በላይ ውጤት አግኝተዋል፡፡ በእነዚህ ክፍሎች የተመዘገበው ውጤት ክልሉ ካሳለፈው የሰላም እጦት አኳያ ሲታይ አበረታች ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን የሰላም ችግሩ በተማሪዎች መማርና ስነልቦና ላይ ያሳደረው ጫና ግምት ውስጥ ገብቶ ማለፊያ ነጥቡ ከ50 በታች ሆኖ እንዲወሰን ተደርጓል፡፡ በዚህ ውሳኔም የተሻለ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ወደሚቀጥለው ክፍል መዛወራቸውን ገልጸዋል፡፡

በተመሳሳይ የ12ኛ ክፍል ብሄራዊ ፈተናም ክልሉ በከፋ የሰላም እጦት ውስጥ ሆኖ የተሰጠ ሲሆን በተፈጥሮ ሳይንስ ወንድ 22 ሺህ 91፣ሴት 22 ሺህ 37 በድምር 44 ሺህ 128 ተማሪዎች ለፈተና ቀርበው ነበር። በማህበራዊ ሳይንስ ደግሞ ወንድ 24 ሺህ 259፣ ሴት 27 ሺህ 492 በድምር 51 ሺህ 751 ተፈትነዋል። በሁለቱም የትምህርት ዘርፎች በጠቅላላው 95 ሺህ 879 ተማሪዎች ሁለቱንም የፈተና አይነቶች ወስደዋል። ፈተናዎች የተሰጡት በወረቀትና በኮምፒውተር ነው፡፡ በኮምፒተር የተፈተኑ አራት ሺህ 88 ተማሪዎች ሲሆኑ 91 ሺህ 659 ተማሪዎች ደግሞ በወረቀት ተፈትነዋል፡፡ ከእነዚህ ተማሪዎች መካከል ወንድ 40 ሺህ 80፣ ሴት 20 ሺህ 51 በድምር 61 ሺህ 31 የሚሆኑት 50 በመቶ እና በላይ ውጤት ያስመዘገቡ ሲሆን አፈጻጸሙም ስድስት ነጥብ አራት በመቶ ነው። ይህም እንደ አገር ከተመዘገበው አምስት ነጥብ አራት አማካይ ውጤት ጋር ሲነጻጸር የተሻለ ነው ማለት ይቻላል፡፡ የእነዚህን ተማሪዎች ውጤት ለማሻሻል ወይም ጥራትን ለማስጠበቅ ከቢሮ ጀምሮ እስከ ትምህርት ቤት ድረስ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ በተለይ ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የአዳር ፕሮግራም በትምህርት ቤቶች እንዲዘጋጅ ተደርጎ ተማሪዎች ሙሉ ጊዜአቸውን በመጠቀም እና መምህራንም ተማሪዎችን በማገዝ በኩል ያደረጉት ጥረት ሁሉ ተደምሮ ለውጤታቸው መሻሻል ያበረከተው አስተፅኦ በመልካምነቱ የሚጠቀስ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ያለፈው አመት የክልሉ ትምህርት ዘመን ከላይ በተገለፀው መልኩ ያለፈ ቢሆንም ቀጣዩ 2017 ዓ.ም ትምህርት ዘመን እንደ ክልል በሰላማዊ ሁኔታ ተጀምሮ እንዲቀጥል ለማድረግ ሰፊ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች ተከናውነዋል። ትምህርት ትውልድ መገንቢያ ተቋም መሆኑን መግባባት ላይ መድረስ



በዞኖች ትምህርት ለትዉልድ የህዝብ ንቅናቄ
ውይይትን ከሚያሳዩ ምስሎች በከፊል(ሰሜን ጎጃም ዞን ደቡብ አቸፈር ወረዳ )

የሚያስችል “ትምህርት ለትውልድ” በሚል መሪ መልዕክት የአመቱ ትምህርት ዘመን መከፈቻን በሁሉም አካባቢዎች ማስጀመርን አላማው ያደረገ ክልላዊ የንቅናቄ መድረክ ተካሂዷል፡፡ ንቅናቄው በድምቀት ከተካሄደ በኋላ ዞኖችና ከተማ አስተዳደሮች የራሳቸውን እቅድ አውጥተው በርካታ የትምህርት ባለድርሻ አካላትን ባሳተፈ መልኩ የየራሳቸውን ንቅናቄ አካሂደዋል፡፡ በተመሳሳይ ወረዳዎችና ከተማ አስተዳደሮችም ከራሳቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር አጣጥመው “ትምህርት ለትውልድ” ንቅናቄን ፈጽመዋል፡፡ ይህ መድረክ በብቃትና በጥሩ ሁኔታ በተመራባቸው አካባቢዎች የተማሪ ምዝገባ አፈጻጸም የተሻለ ሆኖ ታይቷል፡፡ ይህ ደግሞ ህብረተሰቡን አነቃንቆ ያመነበትንና የተግባባበትን ጉዳይ መፈፀም ጥሩ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻል ማሳያ ነው ብለዋል።

ትምህርት ትውልድ የሚታነጽበት ተቋም በመሆኑ ትምህርት ቤቶች በወቅቱ ተከፍተው ስራ እንዲጀምሩ፣አስፈላጊው ሰብአዊም ሆነ ቁሳዊ ግብአት እንዲሟላላቸው ተመክሮ፣ ተዘክሮና አቅጣጫም ተቀምጦ የበጀት አመቱ ትምህርት እንደተጀመረ ተናግረዋል፡፡

በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረትም ለ2017 ዓ.ም ትምህርት ዘመን ቅድመ ዝግጅት በክረምቱ እቅድ ወርዶ ያረጁና የወደቁ ትምህርት ቤቶች ተጠግነዋል። በአዲስ እየተገነቡ ያሉት ትምህርት ቤቶች ቀድመው እንዲጠናቀቁ ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል። በበጎ ፈቃድ ወጣቶች አማካኝነት ለተማሪዎች ማጠናከሪያ ትምህርት እንዲሰጥ የማመቻቸት ስራዎች ተሰርተዋል፡፡ የተማሪ ምዝገባንና የክረምት ቅድመ ዝግጅት ስራዎች ያሉበትን ሁኔታ ለመከታተል በሁሉም ዞኖች የክልል ባለሙያዎች ለ20 ቀናት የመስክ ስምሪት ወስደው ክትትል አድርገዋል፤ ግብረ መልስም ተሰጥቷል።

የተማሪ ምዝገባ እቅድ ለሁሉም ዞኖችና ወረዳዎች ወርዶ ከነሐሴ 2016 ዓ.ም ጀምሮ ተካሂዶ የተሳካ ምዝገባ ተደርጓል፡፡ የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማት ማሟላትንና የተማሪ ምዝገባ ስራዎችን የተመለከቱ ቀስቃሽ ስፖቶች በክልሉ ትምህርት ቢሮ ህዝብ ግንኙነት ተዘጋጅተው በአማራ ሚዲያ ኮርፖሬሽን ቴሌቪዥንና ሬድዮ ለተከታታይ 20 ቀናት በቀን ሁለት ጊዜ እንዲተላለፉ ተደርጓል፡፡ በዚህም የተነሳ ለህብረተሰቡ ሰፊ ግንዛቤ ተፈጥሯል ተብሎ ይገመታል፤ በማለት ለበጀት አመቱ ትምህርት ምዝገባ መሳካት የሚበጁ የቅድመ ዝግጅት ስራዎች መሰራታቸውን አንድ ባንድ ዘርዝረዋል። እነዚህ ሁሉ ጥረቶች መደረጋቸውው በጠንካራ ጎን የሚወሰዱ ቢሆንም በክልሉ ያለው አለመረጋጋት አስተማማኝ በሆነ መልኩ ባለመረጋገጡ በ2017 በጀት ዓመት ተመዝግበው ወደ ትምህርት ቤት መግባት ከሚገባቸወ ከሰባት ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች መካከል የተመዘገቡት ሁለት ሚሊዮን ያህሉ ናቸው፡፡

አቶ ጌታቸው በመጨረሻም ትምህርት የአንድን ሀገር እድገት ለማፋጠንም ሆነ ወደኋላ ለመጎተት የሚጫወተው ሚና ትልቅ መሆኑን በመጠቆም ከድህነትና ኋላቀርነት የምንላቀቀው ትውልዱ በመደበኛ ትምህርት ቤት ገብቶ እንዲማር ሲደረግ ጭምር ነው ብለዋል፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ እድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ አዲስም ሆኑ ነባር ተማሪዎች ወደ ትምህርት ቤት መጥተው መመዝገብና ትምህርታቸውን መከታተል ሲችሉ ነው፡፡ ይህን ዓላማ ለማሳካት ደግሞ የማህበረሰቡ ድርሻ ሰፊ ነው፡፡ ምክንያቱም ትምህርት በአንድ ወገን ማለትም በትምህርት አመራሩና መዋቅሩ ብቻ ውጤታማ አይሆንምና፡፡ በተለይ በአሁኑ ወቅት የመማር ማስተማሩን ሂደት በተማሪ ምዝገባ ማስጀመር ብቻ ሳይሆን እንደ ክልል ያለው የከፋ ሰላም እጦት እጅግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ ስለሚገኝ የተመቸ ሰላም እንዲሰፍን ለማድረግ ዘላቂ መፍትሄ በማምጣት በኩል ሚናቸውን መወጣት





የ2017 ዓ.ም ትምህርት ዘመን የመጀመሪያ ቀን የመጀመሪያ ክፍለ ጊዜ አጀማመርን በከተማ አስተዳደሮችና በዞኖች የሚያሳዩ ፎቶዎች በከፊል( ከግራ ወደ ቀኝ ጎንደር ከተማ አስተዳዳረና ኦሮሞ ብሄረሰብ አስተዳደር)

ይኖርባቸዋል ያሏቸውን ባለድርሻ አካላት ቀጥሎ በቀረበው መልኩ በመዘርዘር አብራርተዋል።

ህብረተሰቡ መተኪያ የሌለው ትልቅ ባለድርሻ አካል ነው። በመሆኑም የትምህርት ስራው በሰላም እንዲከናወን የተለየ ድጋፍና እገዛ ማድረግ አለበት፡፡ ሰላምን ለማረጋገጥ መፍትሄው በህብረተሰቡ እጅ ላይ ነው። አዳዲስ ትምህርት ቤቶችን በመገንባት ፣ያረጁና የወደቁትን በመጠገን፣ የጥራት ደረጃቸውን በማሻሻል በኩል ህብረተሰቡ የሚያሳየውን ተሳትፎ በክልሉ የተመቻ ሰላም እንዲሰፍንና የዚህ በጀት አመት መማር ማስተማር ስራም ያለምንም መስተጓጎል እንዲቀጥል ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሚናውን መወጣት አለበት፡፡ወላጆች እንደ አንድ ባለድርሻ አካል ከምንም በላይ ለልጆቻቸው እድገትና ሰላም የሚጨነቁ ናቸው፡፡ ልጆቻቸው የተሻለ ነገር እንዲኖሩ ይመኛሉ፡፡ ይህ ምኞት እውን የሚሆነው ደግሞ ወላጆች ስለልጆቻቸው መማር ሲከታተሉና ልጆች የሚማሩበት ትምህርት ቤት መሰረተ ልማት የተሟላለትት፣ ደረጃውን የጠበቀና ሰላም የሰፈነበት መሆን ሲችል ነው፡፡ ለዚህ ወሳኝ ጉዳይ ተግባራዊነት የድርሻቸውን መወጣት አለባቸው፡፡ የተማሪዎችን መማርና ሰላም ወሎ መግባት መከታተል፣ ለመምህራንና ትምህርት ቤቶች ግብረ መልስ መስጠት ከወላጆች ይጠበቃል፡፡

መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ባለሀብቶች፣ በጎ አድራጊ ግለሰቦች፣ የልማት ድርጅቶች፣ ወዘተ. የትምህርቱ ዘርፍ የሚመካባቸው አጋር አካላት ናችው። ትምህርት መጠነ ሰፊ የትምህርት መሰረተ ልማት፣ ግዙፍ ግብዓት አቅርቦትና በጀት የሚፈልግ ዘርፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በመንግስትና በህብረተሰቡ አቅም ብቻ ማሳካት ስለማይቻል ክፍተቶችን በመለየት በሚያደርጉት ድጋፍ የክልሉ ትምህርት በብዙ መልኩ እምርታዎችን እያሳየ ቀጥሏል። ይህን ሚናቸውን በአሁኑ ወቅት በክልሉ እየተካሄደ ባለው ጦርነት ምክንያት የተፈጠረው ሰላም እጦት ወደ ነበረበት እንዲመለስና መማር ማስተማር ስራው ያለምንም መስተጓጎል እንዲቀጥል ትኩረት ሰጥተው መሳተፍ እንደሚገባቸው መልዕክት በማስተላለፍ ገለጻቸውን ቋጭተዋል፡፡

እኛም የክልሉ ትምህርት ዘርፍ የታለመለትን ግብ እንዲመታ ከትምህርት መሰረተ ልማት ባሻገር አስተማማኝ ሰላምን በእጅጉ ይፈልጋልና ለዚህ እውን መሆን ጉዳዩ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ሁሉ ትኩረት ሰጥተው ሊረባረቡ ይገባል። የዚህ በጀት አመት ትምህርትም ካለፈው አመት ተግዳሮቶች ተላቆ እንዲቀጥልና ውጤታማ እንዲሆን ሰፊ ጥረት መደረግ እንዳለበት እየጠቆምን አመቱን ሙሉ በትምህርቱ ስራ ውስጥ ተሳትፎ ለምታደርጉ አካላት ሁሉ መልካም የትምህርት ስራ ዘመን እንዲሆንላችሁ እየተመኘን ተሰናበትን።

ሰላም!!

# ስለ አለቃ ገብረ ኃና በጥቂቱ

በፍቃዱ ገድፍ

አለቃ ገብረ ኃና በደቡብ ጎንደር ሀገረ ስብከት በድሮው የደብረታቦር አውራጃ ፎገራ ወረዳ፤ ናብጋ ጊዮርጊስ በተባለው ቦታ በ1 8 1 4 ዓ.ም ተወለዱ። የመጀመርያ ትምህርታቸውን በአካባቢው ከቀሰሙ በኋላ ወደ ጎጃም ተሻግረው ቅኔን ተቀኙ። ከዚያም ወደ ጎንደር ከተማ ተመልሰው ከመምሕር ወደ አብ ወልደ ማርያም ጽዋትወ ዜማ፤ ከባሕታዊ ገብረ አምላክ አቋቋም፤ ከዐቃቤ ስብሃት ገብረ መድሕን ትርጓሜ መጽሐፍትን እንዲሁም ድጓን ተምረዋል። በዚህ የሰፋ እውቀታቸው የተነሣ በ26 ዓመታቸው ጎንደር ሊቀካህናትነት ተሾመው ነበር። በዚህም ሹመት ለሰባት ዓመት ማገልገላቸው ይነገራል። በፍትሐ ነገሥት ሊቅነታቸው ደግሞ በዳኝነት እየተሰየሙ አገልግለዋል። አለቃ ገብረ ኃና ጨዋታ አዋቂነታቸው እየታወቀ የመጣው በዚህ ወቅት ነበር።አጼ ቴዎድሮስ ሥልጣኑን ሲይዙ አለቃን በቤተ መንግሥት አገኟቸው። አለቃ የቤተ መንግሥቱን ሰዎች በቀልዳቸው ሸንቆጥ ስለሚያደርጉ መስማማት አልቻሉም ነበር። እንዲያውም ዐጼ ቴዎድሮስ "ገብረ ኃና ፍትሐ ነገስቱን ጻፍ፤ ፍርድ ስጥ .. ገንዘብ ያውልህ፤ ቀልድህን ግን ተወኝ።" ሲሉ ተናግረዋቸው ነበር ይባላል። አለቃ ግን አላቆሙም።

### የአለቃ የልጅ ልጅ

ነገሩ የሆነው ፎገራ ውስጥ ሲሆን በደርግ ዘመን ነው። ካድሬው ህዝቡን ሰብስቦ ስለ መንደር ምስረታ አስፈላጊነት ሲያብራራ "በመንደር ከሰፈራችሁ ውሃና መብራት በየቤታችሁ ይገባላችኋል" እያለ ከቀሰቀሰ በኋላ የህዝቡም ተቃውሞ አዳማጭ ሳያገኝ ሰፈሩ ሜዳ ላይ ተሰርቶ ሕዝብ ሰፈረ። ክረምት ሲመጣም ጣና ሐይቅ እንደተለመደው የፎገራን ሜዳ ቤቴ ብሎ ሲያጥለቀልቀው ህዝቡ ወደ አካባቢው ከተሞች ተሰደደ። በዛን ወቅት የአለቃን የልጅ ልጅ ጋዜጠኛ አግኝቶ ስለ ሁኔታው ሲያነጋግረው "ያው በካድሬው እንደተነገረን ውሃው በየቤታችን ገብቷል መብራቱ ብቻ ነው የቀረው" ብሎ አስተያየቱን ሰጠ።

### ጎመን እያበሰልሁ ነው

በእመቤታችን በፍስለታ ጾም አለቃ ቤተክርስቲያን አገልግለው ሲመለሱ ባለቤታቸው ማዘንጊያ የሚበላ ነገር በጎመን ይሰጧቸዋል ጎመኑ አልበሰሎም ኑሮ ከምግብ በኂላ አለቃ ጥዳቸውን ወደሳቱ ጠጋ አድርገው ያሻሻሉ። ማዘንጊያ ነገሩ ገርሟቸው አለቃ ምን እያደረጉ ነው ይሏቸዋል አለቃም በአሽሙር ጎመኔን እያበሰልሁ ነው አሉ ይባላል።

### አይ ጎራዴ አይ አስተጣጠቅ

አንድ የሚኒልክ መኮንን ስልብ ነበሩ ይባላል። መኮንኑ አንድ የጀግንነት ስራ ይሰሩና ሙሉ ትጥቅ ከነልብሱ ይሸለማሉ። አለቃን ያገኟቸውና "አለቃ እንዴት ነው? " "አላማረብኝም" ይላሉ።አለቃም መልሰው "አይ አስተታጠቅ አይ አለባበሥ አይ ጎራዴ አይ ጎራዴ አይ ጎራዴ" ይላሉ። ሌሎች መኳንንት መኮንኑን አለቃ ምን አሉህ? ይሉታል አደነቁኝ አይ አስተታጠቅ አይ ጎራዴ አሉኝ ይላል።መኳንንቱም ምን አደነቁህ ሰደቡህ እንጂ ስልብ ስለሆንክ ጎራዳ ነህ — አይ ጎራዴ -የኔ ጎራዳ ነው ያሉህ ብለው አብግነውት አለቃን ካልገደልኩ ብሎ በገላጋይ ነው አለቃ የተረፉት አሉ።

### እንደምን አደራችሁ

አለቃ ሀሳባቸውን "በሰምና ወርቅ" በመግለጽ ጥበባቸው ተወዳዳሪ የላቸውም ይባላል። ታዲያ አንድ ቀን አንድ አውቃለሁ ባይ ሰውዬ ስለእርሳቸው ቅኔያዊ አነጋገር ምንም ቦታ እንደማይሰጥና በቅኔ ቢሰድቡት እርሱ ደግሞ ከዚያ በላይ በቅኔ መልሶ ሊሰድባቸው እንደሚችል ጉራውን ይነዛል። ጉራውንም የሰሙት ሰዎች አይ አንተ ሰው! ስለማታውቃቸው ይሆናል እንጂ የሚቻሉ አይደሉም። ይሰድቡሀል። ለማንኛውም ከፈለካቸው ወደገበያው መሄጃ መንገድ አከባቢ ስለማይታጡ ብቅ ማለት ትችላለህ ይሉታል። ሰውዬውም ቢያገኛቸው ለቅኔያቸው የሚሰጠውን መልስ እያሰላሰለ አህያውንም እየነዳ ወደ ገበያ ሲሄድ ያገኛቸዋል። ከዚያም ሰውዬው "አለቃ እንደምን አደሩ?" ይላቸዋል። አለቃም ትኩር አድርገው ያዩትና የተንኮል ሰላምታ መሆኑን በመረዳት "እግዚአብሄር ይመስጌን ደህና ነኝ! እናንተስ ደህና አደራችሁ ወይ?" ብለው በትህትና ለሰላምታው መልስ ሰጥተው ይሸኙታል። ሰውዬውም ስላልተሰደብኩኝ መስደብ የለብኝም ብሎ እየተኩራራ ይመለስና እነዚያን ሰዎች ያገኛቸዋል። ኧሃ ከአለቃ ጋር ተገናኛችሁ? ምንስ ብለው ሰደቡህ? ሲሉት እርሱም አይ ምንም አልሰደቡኝም እንዲያውም በትህትና ሰላምታ ተለዋወጥን። እኔን ሊሰድቡኝ አይችሉም ብያችሁ የለም? አለ። እስቲ እንዴት ነበር የተባባላችሁት ሲሉት አይ እኔ አለቃ

እንዴት አደሩ ሰላቸው እሳቸውም በትህትና አንገታቸውን ዝቅ አድርገው “እግዚአብሄር ይመስጌን እናንተስ እንዴት ናችሁ ነው” ያሉኝ አላቸው። ሰዎቹም ካንተ ጋር ሌላ ሰው ነበረ ወይ ሲሉት ኸረ የለም አህያዬን እየነዳሁ እሄድ የነበርኩ እኔ ብቻ ነበርኩኝ ሲላቸው አይ ወንድሜ ! አንድ ሰውማ እንዴት አደራችሁ አይባልም አንተን ከአህያህ ጋር አንድ አድርገው በመቁጠር ነው እንዴት አደራችሁ ያሏችሁ ብለው የሰውየውን መሸነፍ እና አህያ መባል አበሰሩለት አሉ።

**አለቃ ገብረ ኃና ሞቱ**

አለቃ በጣም ቸገራቸውና ልጃቸውን ሂድና ንጉስ ሚኒሊክን አባቴ ሞቶ ግን ተስካሩን የማወጣበት ገንዘብ የለኝም ብለህ ገንዘብ ተቀብለህ ና ብለው ላኩት። ልጅም እንደተባለው ወደ ቤተመንግስት ሂዶ ያባቱን ከዚህ አለም በሞት መለየት ነግሮ እንደተባለው ገንዘቡን ይጠይቃል። ምኒሊክም እጅግ በጣም አዝነውና አልቅሰው ገንዘቡን ሰጥተው ይልኩታል። አለቃም ችግራቸውን ከተወጡ በኋላ ምኒሊክን ሊያዩ ጉዞ ወደ አዲስ አበባ ያቀናሉ። በቤተመንግስቱም ያያቸው በመገረም እን…ዴ? አለቃ ሞተው አልነበር በማለት እየተገረሙ ለምኒሊክ ሊነግሩ ተጣደፉ። ሚኒሊክም ሲያዩአቸው ገብረኃና ሞተህም አልነበር ቢሏቸው አለቃም እንደርሶ የሚስማማኝ ንጉስ ባጣ ተመልሼ መጣሁ ብለው ንጉሱን አሳቋቸው አሉ።

**ሃድጎ -አህያ ሽራህያ**

ጋዜጠኛው አረፋይኔ ሀጎስ ስለ አለቃ ገብረ ኃና መጽሀፍ ጽፏል። ታዲያ አለቃ ከአጼ ተዎድሮስ ጊዜ ጀምሮ የነበሩ የቤተክርስቲያን ምሁር እንደሆኑ ነው መጽሀፉ የሚያወራው።ከጊዜው ቀልዳቸው አንዱ እንዲህ ይላል። በአጼ ተዎድሮስ ቤተመንግስት ሀድጎ የሚባል ባለሟል ነበረ ታዲያ ምንም እንኳን ንጉሱ ቀልድ የማያውቁ ኮስታራ ቢሆኑም አለቃ ግን መኮመኪያ ምክንያት አላጡም። እናም ሀድጎን ባገኙት ጊዜ ሁሉ ሀድጊ ብለው ነበር አሉ የሚጠሩት። አህያ ለማለት።ሀድጎም መረረውና ጃንሆይ ዘንድ ከሰሳቸው።. ንጉሱ አለቃን አስጠርተው ለምን ሀድጊ እያሉ እንደሚሳደቡ ቢጠይቋቸው አይ ጃንሆይ እኔ “አህያ ሽራህያ” እያልኩ ስጸልይ ሰምቶኝ እንጂ አልሰደብኩትም ብለው በብልሀት አመለጡ።

አለቃ ገብረ ኃና_በጣም አጭር — ድንክዬ ሰው ናቸው:: ሚስታቸው ወይዘሮ ማዘንጊያሽ ደግሞ ሲበዛ 1ሜትር ከ80 ናቸው። መንገድ ውለው ወደቤታቸው ሲመለሱ ወይዘሮ ማዘንጊያሽ ሠማዩን አይተው አለቃ ዝናብ ሊዘንብ ነው መሰለኝ ይሏቸዋል። ከዚያ አለቃ ከኋላቸው ኩስ ኩስ እያሉ ሲመልሱላቸው! “እኔ ምን አውቃለሁ ለሰማዩ ቅርቡ አንቺ ነሽ” አሏቸው ይባላል።

**ገብተሽ አልቀሽ**

አንድ ቀን ከወዳጆቻቸው ዘንድ ድግስ ተጠርተው ሄደው እዚያ ውለው ወደ ቤታቸው ሲመጡ አሽከራቸው በር ሲከፍት አስቀደመው አለቃ ገብተው የባለቤታቸውን መግባት ሲጠባበቁ ትንሽ ዘግየት ስላሉ “እባክሽ ገብተሽ ገብተሽ አልቀሽ እንደሆን በሬን ልዝጋበት” አሉ። የቁመታቸውን መርዘም መናገራቸው ነው።

**ደርቆ ተንጣጣ**

አንድ ሰሞን አለቃ በጣም ቆንጆ ልጅ ያገባሉ። ከዚያም ያው እንደ ባህል ወጉ ልጂቱ እሳቸው ጋ ልታድር ቤታቸው ትሄዳለች። እናም ቀኑ ተገባዶ ማታ ላይ አለቃ ቆጥ ላይ ወጥተው ሲጠብቋት እሷ ማታ ወደ ቤተሰቦቿ ከድታ ልትሮጥ ከቤት ስትወጣ ውጪው እንደአጋጣሚ ዝናባማ ስለነበር አድልጧት ትወድቅና ተመልሳ ቤት ትገባለች። ቤት ገብታም ምድጃ ዙሪያ ተቀምጣ ልብሷን ስታደርቅ ሳት ይላትና ጡጦ ታደርጋለች። ይህን የሰሙት አለቃ “አንቺ አትተኚም?” ይሏታል። እሷም “እስኪ ይቆዩ ልብሴ ምጥጥ ምጥጥ ይበልልኝ” ትላለች። እሳቸውም እሺ ብለም ዝም ሲሉ ልጂቱ አሁንም ደግማ ዛጥ ታደርጋለች።በሁኔታው የተቆጡት አለቃ በስጨት ብለው “አንቺ አትተኚም?” ሲሏት። እሷ “እስኪ ይቆዩ…ልብሴ ይድረቅ ትላለች።” ከዚያም አለቃ ቀጥለው “ኸረ …ሌዲያ …ልብስሽ ደርቆማ እየተንጣጣ” ብለው ባሽሙር ጠቅ አረጓት ይባላል።

**ምንጭ፡-** አየር ሜዳ ባህር ዳር ፌስቡክ ገፅ (አለቃ ገብረሃና እና አስቂኝ ቀልዶቻቸው በአረፈ አይኔ ሀጎስ)



አረንጓዴ አሻራ (አዊ ብ/እስተዳደር  እና አርጎባ ወረዳ )



በፌርዌል መድሐኒት ፋብሪካ የስራ ጉብኝት



